
# መጽሐፈ ዲድስቅልያ

## ዘአበዊነ ሐዋርያት



አሳታሚ፡- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፳፻ፀ ዓ.ም.



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ (ዶ/ር)

ቀዳማዊ፣ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ

ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና

የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት

# መ ግ ለ ጫ

ንሕነሰኬ ኢንክል ክቢቶቶ ለዝንቱ ነገር"
እኛስ ይህንን ነገር ልንሠውረው አንችልም።
(ግብረ ሐዋርያት ፬ ፡ ፳)

በብሂለ አሶ ፡ "በቃል ያለ ይረሳል፣ በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል" እንደተባለው በየዐረፍተ ዘመኑ በልብ የታሰበውን፣ በቃል የተነገረውን፣ በተግባር የተፈጸመውን፣ ማንኛውንም ክንውን በጽሑፍ አስፍሮ፣ የተጻፈውንም በክብር ጠብቆና አቆይቶ ለትውልድ ማስተላለፍ በየዐረፍተ ዘመኑ ከሚነሳው ትውልድ ሁሉ የሚጠበቅ ታሪካዊ ግዴታ ነው።

በመሆኑም ጥንታዊትና ታሪካዊት፣ እንዲሁም ብሔራዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከተቀበለቻቸው አምላካውያት ሰማንያ ወአሐዱ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስምንቱ የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው።

**<u>በዝርዝር ሲገለጹም</u>** :-

- ❖ ሥርዓተ ጽዮን ፤
- ❖ ትእዛዝ፤
- ❖ ግጽው፤
- ❖ አብጥሊስ፤
- ❖ ፩ኛ መጽሐፈ ኪዳን፤
- ❖ ፪ኛ መጽሐፈ ኪዳን፤
- ❖ ቀሌምንጦስ፤
- ❖ ዲድስቅልያ

በመባል ይታወቀቀሉ።

ሰዋቢነት የሚቀርበውም "ለመጻሕፍተ ቀኖናትሰ ቀዳሚሆሙ ቀኖና፣ "ዘሠርዕዋ ሐዋርያት። ወእሙንቱ እንዘ ጉቡአን በጽርሐ ጽዮን፣ እምድኅረ ዕርገት፣ ወርደተ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌሆሙ ወእምቅድመ ይዘረዉ በእንተ ስብከት" የሚለው ገጸ ንባብ ሲሆን፣ ትርጓሜውም የቀኖና መጻሕፍት መጀመሪያቸው፣ ሐዋርያት የሠሩዋት ናት። እነርሱም ከዕርገትና መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ከወረደ በኋላ ፣ ለስብከተ ወንጌል ከመበተናቸው አስቀድሞ በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው ሳሉ የሠሩዋት ናት የሚለው ነው። (መቅድመ ፍትሐ ነገሥት ገጽ ፲፪ ፫ራግራፍ ፫።)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "አኃዊነ! ንኤዝዘክሙ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ተገሐሥሙ ለኵሉሙ ቢጽ እለ የሐውሩ በትምይንት፣ ወአኮ በሥርዐት ዘሠራዕናሆሙ" 2ኛ ተሰ 3:6)

ወንድሞቻችን! በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናገዛችኋለን፤ በሠራንላቸው ሥርዐት ያይደለ በተንኮል የሚሔዱትን ሰዎች ሁሉ ተለዩአቸው። በሚለው ቃለ ሐዋርያ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ቤተሰቦችዋን፣ የእምነት ተከታዮችዋ፣ ምእመናንን የምታስተዳድርባቸው የሕግና የሥርዐት መጻሕፍት ናቸው።

ከስምንቱ የሥርዐት መጻሕፍት አንዱ "ዲድስቅልያ" የተሰኘው የሥርዓት መጽሐፍ ነው። ዲድስቅልያ ማለትም ፣ ቃሉ የጽርኢ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም ትምህርት ማለት ሆኖ፣ ከላይ እንደ ተገለጸው ቅዱሳን ሐዋርያት ከሐዲስ ኪዳን ለትምህርት አውጣጥተው ያዘጋጁት ነው።

"መቅድመ መሐርምሙ ለውሉድክሙ መጽሐፈ ሲራክ ወሰሎሞን፣ ወመዝሙረ ዳዊት ወዲድስቅልያ" እንደተባለው የሥርዐት መጽሐፍ ብቻ ላይሆን ለትምህርተ ሕግናትም ጠቃሚ እና አስፈላጊም ነው። ዲድስቅልያ የተሰኘው ይህ የሥርዐት መጽሐፍ በግዕዝ አናቅጽ የተከፈለ ሲሆን፣ ከቀድሞ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከተላለፉልን የሥርዓት መጻሕፍት አንዱ ስለሆነ ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ ፫፡፩-፰ ላይ "ቦ ለኵሉ ዘመን፣ ወቦ ጊዜ ለኵሉ ምግባር ዘታሕተ ፀሐይ" ለሁሉ ዘመን አለው፣ ከፀሐይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው፣ በማለት እንደተናገረው፣ ቀደም ሲል በቁም ጽሕፈት ተጽፎ፣ በቤተ መጻሕፍት ወመዛክር በክብር ተጠብቆ፣ አንድ ሰራሱ ሆኖ ተቀምጦ የነበረው መጽሐፈ ዲድስቅልያ ሰመሳው አብያተ ክርስቲያናት፣ ለትምህርትና ለምርምር ይበጅ ዘንድ፣ በማሳተሚያ ድርጅታችን ተዘጋጅቶ፣ በሊቃውንት ጉባኤ ተመርምሮ፣ ታትሞ እንዲሰራጭ ማድረጋችንን ስናበሥር መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል።

"አምላከ ቅዱሳን ሐዋርያት ኢትዮጵያን ይባርክ"

አባ ጳውሎስ ዶ/ር ቀዳማዊ፣

ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወአጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት፣

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና ፣

የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት

ሐዋርያት የሰማርያን ሰዎች ባስ ተማሩ ጊዜ ሲሞን መሠርይ እጃ ቸውን በጫኑበት ላይ፣ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ፣ ተአምራት ሲደ ረግ፣ ድውያን ሲፈወሱ አይቶ ይህ ተአምራታቸው የሥራይ መስሎት እኔም እጁን በጫንኩበት መንፈስ ቅዱስ እንዲአድር፣ተአም ራት እንዲደረግልኝ አድርጉኝ ብሎ በሥራይ የሰበሰበውን ብዙ ወርቅ ብር አምጥቶ ለሐዋርያት ሰጣ ቸው፤ ጴጥሮስ ወርቅክ ወብሩርክ ይኵንክ ለክ ለሕርትምና፤ ወርቅህ ብርህ ላንተ ለጥፋትህ ይሁንኽ፣ ይመስለክኑ ዘበወርቅ ትሣየጦ ለጸጋ እግዚአብሔር ፣ አንዱን አካል ወልድን ይሁዳ ሸጠው፤ እኛ ደግሞ አንዱን አካል መንፈስ ቅዱስን የምን ሸጥልህ በወርቅ የምትገዛው ይመስልሃልን፣ አል ብክ ክፍል ውስተዝ ነገር ፣ መንፈስ ቅዱስን ማሳደር ፣ አን ድም ከኛ ጋር እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የለህም፣ በጽኑ ክህደት ተይዘህ አይሃለሁና አለው፤ እሱም ይህ ሁሉ እንዳይደረግብኝ ጸልዩልኝ አለ።

ከዚህ የማይሆንለት ቢሆን አንጾ ኪያ ወርዶ ያስት ጀመረ፣ ለጴጥሮስ ደቀ መዛሙርትህን አሳተ ብለው ነገሩት ፣ ዮሐንስን አስከትሎ አንጾኪያ ወረደ፣ ሲሞን መከራከር የማይቻለው ቢሆን ሮም ወረደ ፣ ከዚያም ሄዶ አልተወም፣ ያስታል ብለው ነገሩት፣ ጴጥሮስ ዮሐንስን አስከትሎ ወርዶ ቅብውን በአንቀጸ ሮም አግኝተው ፈውሰውት ገብተዋል ። ተአምራትስ ይሕታ (ይህ ነው) ብለው ሕዝቡ ወደ እነሱ ተሳቡ፣ ለመሥዋዕት የቀረበ ላም ነበር ሹክ፣ ሹክ ቢለው ከሁለት ተከ ፈለ ፣ ከሚዛን ቢአገቡት ትክክል ሁኗል፣ ሚዛኑ የዓይን ነው። ተአምራትስ ይሕታ (ይህ ነው) ብለው ወደ ሲሞን ተሳቡ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ቢባርከው ተነሳ፣ ጠርተህ አምጣው አለው በቃል ሰብአዊ ጠርቶ እያዳፋ እያጋፋ አመጣው ፤ ተአምራትስ ይሕታ (ይህ ነው) ብለው ወደ ሐዋርያት ተሳቡ፣ በሬ አስነሥቶ ማስቀ ባጠር ቁም ነገር ነውን ብሎ አጋንንትን በምስሐቡ ስቦ ያንተ ሀብት ይህ ነው፣ አንተን ቅስና፣ አንተን ዲቁና ሹሜሃለሁ ብሎ ዐረግሁ አለ፣

ዮሐንስ ቅዱስ ጴጥሮስን አበ ዓለም ዝም ትላለህን አለው፣ ተወው በእምር ከፍ ይበል አለው፣ በእምር ከፍ ሲል ቢያማትብበት አጋንንት ጥለውት ሸሹ፣ ወድቆ ተንቆጫቁጮ ሙታል።

ከዚያ የነበሩት የእርሱ ደቀ መዛ ሙርትም ብዙ ክህደትና ኑፋቄ አፍልቀዋል።

በዚህ ምክንያት አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፣ ሰባ ሁለቱ አርድዕት፣ ንዋይ ጎሩይ ጳውሎስ፣ ያዕቆብ እጉሁ ለእግዚእነ ሁነው በኢየሩ ሳሌም ተሰብስበው አርባ ሦስት አንቀጽ፣ ዲድስቅልያ ተናግረዋል። ይህንኑም ጌታ ባረገ በሃያ ሁለት ዓመት በፊልጵስዩስ ሕንፀተ ቤተ ክርስቲያንን ካሳያቸው፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ካስተማራቸው በኋላ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደአንድ ልብ መካሪ ሁነው ወስ ነው ጽፈው ለቀሌምንጦስ ሰጥተ ውታል፣ ከዚያ አንሥቶ በመምህ ራን ቃል ሲነገር ከዚህ ደርሷል። ይኸውም ለኛ ምክር እዝናት ሊሆን ተጽፎልናል፣

መጽሐፉ ባዘዘው ሥርዓት ብንጸና ተስፋችንን ካለኝታችን ፍጻሜ ከኢየሱስ ክርስቶስ እናገኝ ዘንድ፣ ወሎሱ ዘተጽሕፈ ለተግሣጸ ዚአነ ተጽሕፈ ፣ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎተ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ አንዲል፣

ልመናቸው በረከታቸው በወዳ ጃቸው በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ወፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ይደ ርና ንጹሓን ክቡራን የሚሆኑ አባቶች ሐዋርያት ያስተማሩት የዲ ድስቅልያ ትምህርት ይህ ነው።

# ማውጫ


| አንቀጽ | ገጽ | አንቀጽ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| አንቀጽ ፩. ዲድስቅልያ ብም ህርተ አበው ቅዱሳን ሐዋ ርያት፤ | ገጽ ፩ | አንቀጽ ፩. የቅዱሳን አበው ሐዋርያት (ትምህርት) ዲድስቅልያ፤ | ገጽ ፩ |
| አንቀጽ ፪. በእንተ ከመመ ፍትው ለአብዕ ልት ይጎሥሡ አእምሮ ረባሕ እመጻሕፍት ። | ገጽ ፲፩ | አንቀጽ ፪. ባለጸጎች በመ ንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን ጥቅም ከመጻሕፍት ይፈልጉ ዘንድ እን ዲገባ፤ | ገጽ ፲፩ |
| አንቀጽ ፫. በእንተ ከመ መፍትው ይት አዘዛ አንስት ለአምታቲሆን | ገጽ ፲፯ | አንቀጽ ፫. ሴቶች ለባሎቻ ቸው መታዘዝ እንደ ሚገባቸው፤ | ገጽ ፲፯ |
| አንቀጽ ፬. በእንተ ኤጲስ ቆጶስ ወቀሲስ ወዲያቆናት፤ | ገጽ ፳፪ | አንቀጽ ፬. ስለ ኤጲስ ቆጶስ ስለ ቄስና ስለ ዲያቆናት አገልግሎት፤ | ገጽ ፳፪ |
| አንቀጽ ፭. በእንተ ከመ ኢመፍትው ለኤ ጲስ ቆጶስ ይስ ማዕ ነገረ ውዴት፤ | ገጽ ፴፯ | አንቀጽ ፭. ኤጲስ ቆጶስ የነገር ሥራን መቀበ በል እንደማይገባው፤ | ገጽ ፴፯ |
| አንቀጽ ፮. በእንተ ኤጲስ ቆጶሳት ይትወክፉ ንስሐሆሙ ለእለ ይትመየጡ ። | ገጽ ፵፪ | አንቀጽ ፮. ኤጲስ ቆጶሳት በፍቅርና በቅንነት የሚመለሱትን ንስሐቸውን መቀ በል እንዳለባቸው፤ | ገጽ ፵፪ |
| አንቀጽ ፯. በእንተ ከመ ኢመፍትው ንጉ ሥፅ ወኢመነሂ፤ | ገጽ ፵፭ | አንቀጽ ፯. ጥፋተኛ መሆኑ ሳይመሰከርበት ምንም መቀጣት እንደሌለበት ። | ገጽ ፵፭ |
| አንቀጽ ፰. በእንተ ከመ መፍትው ይብኡ መባዓ፤ | ገጽ ፶፪ | አንቀጽ ፰. ምዕመናን ባሳ ቸው መጠን ለቤ ተክርስቲያን መባ ያገቡ ዘንድ እንዲገባ፤ | ገጽ ፶፪ |

# ማውጫ


| አንቀጽ | ገጽ | አንቀጽ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| አንቀጽ ፱. በእንተ ከመ ኢመፍትው ዲያቆን ይግበር ወኢምንተኒ ዘእንበለ መዓሐተ ኤጲስ ቆጶስ፤ | ገጽ ፻፩ | አንቀጽ ፱. ዲያቆን ያለ ኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ ምንም ምን ማድ ረግ እንዳይገባው፤ | ገጽ ፻፩ |
| አንቀጽ ፲. በእንተ ከመ መፍትው ኤጲስ ቆጶስ ያመክር ወይ ጠይቅ ኵሎ ነገረ፤ | ገጽ ፻፲ | አንቀጽ ፲. ኤጲስ ቆጶስ ነገርን ሁሉ መርምሮ ይረዳ ዘንድ እንደ ሚገባ፤ | ገጽ ፻፲ |
| አንቀጽ ፲፩. በእንተ ከመ መፍትው ለክርስቲያን ይጎድጉ ወትረ ለቢያመ አበሳ፤ | ገጽ ፻፵፬ | አንቀጽ ፲፩. ክርስቲያኖች ዘወትር የወንድሞቻ ቸውን በደል ይቅር ይሉ ዘንድ እንዲገ፤ | ገጽ ፻፵፬ |
| አንቀጽ ፲፪. በእንተ ከመ ኢመፍትው ለክርስ ቲያን ይባሉ ውስተ ማኅደረ ነኪ. ራን፤ | ገጽ ፻፶፭ | አንቀጽ ፲፪. ክርስቲያኖች በሃይማኖት ወደ ማይ መለሷቸው ቤት ጨዋታ ለማየት፤ ዘፈን ለመስ ማት መሔድ እንዳይ ገባቸው፤ | ገጽ ፻፶፭ |
| አንቀጽ ፲፫. በእንተ መበ ሊታት ዘኢለቦን ምት | ገጽ ፻፷፩ | አንቀጽ ፲፫. ባል ስለሌ ላቸው ሴቶች፤ | ገጽ ፻፷፩ |
| አንቀጽ ፲፬. በእንተ ከመ ኢመፍትው ያጥምቃ አንስት ፤ | ገጽ ፻፷፭ | አንቀጽ ፲፬. ሴቶች ያጠ ምቁ ዘንድ እንደ ማይገ፤ | ገጽ ፻፷፭ |
| አንቀጽ ፲፭. በእንተ ከመ ኢመፍትው ይግበር ሕዝባዊ ግብረ ክህነት፤ | ገጽ ፻፷፯ | አንቀጽ ፲፭. ሕዝባዊ የክ ህነትን ሥራ ይሠራ ዘንድ እንደማይገ፤ | ገጽ ፻፷፯ |
| አንቀጽ ፲፮. በአንተ መአ ስብ፤ | ገጽ ፻፸ | አንቀጽ ፲፮. ስለፊት ሴቶች (መበለታት) የሚናገር፤ | ገጽ ፻፸ |
| አንቀጽ ፲፯. በእንተ ዕንለ ማውታ፤ | ገጽ ፻፸፯ | አንቀጽ ፲፯. አባት እናት ስለሞቱባቸው፤ | ገጽ ፻፸፯ |

# ማውጫ


| አንቀጽ | ገጽ | አንቀጽ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| አንቀጽ ፲፮. በእንተ ከመ መፍትው ይተክዙ ኤጲስ ቆጳሳት በእንተ እበራት ወዕንለ ማውታ፤ | ገጽ፻፹፮ | አንቀጽ ፲፯. ኤጲስ ቆጳሳት እናት አባት ለሞቱ ባቸው ልጆችና ባል ቴቶች ማዘንና መር ዳት እንደሚገባቸው፤ | ገጽ ፻፹፯ |
| አንቀጽ ፲፱. በእንተ ከመ መፍትው መለስብ ወመበለታት ይን ሥኣ ዘተጸገዋ በአ ቴት፤ | ገጽ ፻፺ | አንቀጽ ፲፱. ባሎቻቸው የሞቱባቸውና ባልቴ ቶች የሚሰጣቸውን ዕርዳታ በምስጋና መቀ በል እንዳለባቸው፤ | ገጽ ፻፺ |
| አንቀጽ ፳. በእንተ ከመ መፍትው ኤጲስ ቆጳስ ይለቡ ነሚአ መባዕ፡ | ገጽ ፻፺፩ | አንቀጽ ፳. ኤጲስ ቆጳሱ መባ የሚቀበላቸ ውን ሰዎች ሥነ-ምግባር ማወቅ እንዳለበት፤ | ገጽ ፻፺፩ |
| አንቀጽ ፳፩. በእንተ ከመ መፍትው ይገ ሥው አበው ውሉ ዶሙ፤ | ገጽ ፻፺፫ | አንቀጽ ፳፩. ወላጆች ልጆ ቻቸውን ይመክሩ ይገሥው ዘንድ እን ዲገባ፤ | ገጽ ፻፺፫ |
| አንቀጽ ፳፪. በእንተ ከመ መፍትው ይተ ሐቱ አግብርት ለአ ጋዕዝቲሆሙ፤ | ገጽ ፻፺፱ | አንቀጽ ፳፪. አገልጋዮች ለአሳዳሪዎቻቸው በግብረገብነት መታ ዘዝ እንዳለባቸው፤ | ገጽ ፻፺፱ |
| አንቀጽ ፳፫. በእንተ ከመ መፍትው ለደና ግል ይብጽኣ ርእሶን ዘእ ንበለ ያመከራ ነፍሶን፤ | ገጽ ፪፻ | አንቀጽ ፳፫. ደናግል ከል ባቸው አስበው ሳይ መክሩ በድንግልና ለመኖር እንዳ ይሳሉ፤ | ገጽ ፪፻ |
| አንቀጽ ፳፬. በእንተ ሰማ ዕት አለ ወሰ ምሙ ነበ ምኵናን፤ በእንተ በዓላት ወፋሲካ | ገጽ ፪፻፩ | አንቀጽ ፳፬. ስለ በዓላትና ፋሲካ መከራ ስለሚ ቀበሉ ሰማዕታት፤ | ገጽ ፪፻፩ |

# ማውጫ


| አንቀጽ | ገጽ | አንቀጽ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| አንቀጽ ፳፭. በእንተ ትን ሣኤ ሙታን፤ | ገጽ ፪፻፲፫ | አንቀጽ ፳፭. ስለ መታን መነሣት፤ | ገጽ ፪፻፲፫ |
| አንቀጽ ፳፮. በእንተ ለማዕት፤ | ገጽ ፪፻፳፫ | አንቀጽ ፳፮. ስለ ለማ ዕታት የሚናገር፤ | ገጽ ፪፻፳፫ |
| አንቀጽ ፳፯. በእንተ ከመ ኢመፍትው ይባሉ ክርስቲ ያን ውስተ ቤተ ተውኔት፤ | ገጽ ፪፻፳፬ | አንቀጽ ፳፯. ክርስቲያኖች ወደ ዘፈን፤ ወደ ጨዋታ ቤት መሔድ እንደ ማይገባቸው፤ | ገጽ ፪፻፳፬ |
| አንቀጽ ፳፰. በእንተ ከመ ኢመፍትው ክርስቲ ያን ይምሐሉ በስመ አማልክት መኢጋን ንት፤ | ገጽ ፪፻፳፭ | አንቀጽ ፳፰. ክርስቲያኖች በጣዖትና በአጋንንት ስም መማል እንደ ማይገባቸው፤ | ገጽ ፪፻፳፭ |
| አንቀጽ ፳፱. በእንተ ከመ ኢመፍትው ይዕ ቀቡ ወይፈጽሙ ዕለተ በዓላት በፍ ሥሐ መንፈሳዊት፤ | ገጽ ፪፻፳፱ | አንቀጽ ፳፱. የበዓላት ቀኖ ችን በመንፈሳዊ ደስታ ይጠብቁ ዘንድ እንደሚገባ፤ | ገጽ ፪፻፳፱ |
| አንቀጽ ፴. በእንተ ከመ መፍትው ንለቡ ክር ስቲያን ገቢረ ዕለተ ፋሲካ፤ | ገጽ ፪፻፴፪ | አንቀጽ ፴. ክርስቲያን የፋሲካ በዓል የሚ ደረግበትን ዕለት መገ ንዘብ እንደ ሚገባን፡ | ገጽ፪፻፴፪ |
| አንቀጽ ፴፩. በእንተ ፍል ጠተ ዕልዋን ወመና ናፍቃን፤ | ገጽ ፪፻፴፫ | አንቀጽ ፴፩. ከዳተኞች ንና መናፍቃንን ስለመለየት፤ | ገጽ ፪፻፴፫ |

# ማውጫ


| አንቀጽ | ገጽ | አንቀጽ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| አንቀጽ ፴፪. በእንተ ዘከመ አብአ ሰይጣን ፍል ጠተ፤ | ገጽ ፪፻፷፪ | አንቀጽ ፴፪. ሰይጣን በቤተክርስቲያን ውስጥ ክርክርንና መለያየትን ስለማስ ገባቱ፤ | ገጽ ፪፻፷፪ |
| አንቀጽ ፴፫. በእንተ ርትዕት ሃይማኖት ወቅድስት ሥላሴ፤ | ገጽ ፪፻፷ | አንቀጽ ፴፫. ስለ ቀናች ሃይማኖትና ስለ ቅድስት ሥላሴ፤ | ገጽ ፪፻፷ |
| አንቀጽ ፴፬. በእንተ ከመ መፍትው ይጸልዩ ወይስአሉ ወይ ዘምሩ ላዕለ እለ አዕረፉ፤ | ገጽ ፫፻፯ | አንቀጽ ፴፬. ስለሞቱ ሰዎች ይጸልዩና ይዘምሩ ዘንድ እን ዲገባ፤ | ገጽ ፫፻፯ |
| አንቀጽ ፴፭. በእንተ ፃማ ወአኮ ቈት፤ | ገጽ ፫፻፲ | አንቀጽ ፴፭. ስለ መን ፈላዊ ምስጋናና ደኅም፤ | ገጽ ፫፻፲ |
| አንቀጽ ፴፮. በእንተ ሜሮን፤ | ገጽ ፫፻፲፰ | አንቀጽ ፴፮. ስለ ሜሮን፤ | ገጽ ፫፻፲፰ |
| አንቀጽ ፴፯. በእንተ ቅኔ ሠራዊት መንፈሳው ያን፤ | ጽ ፫፻፳፬ | አንቀጽ ፴፯. ስለ መን ፈላውያን መላእክት አገልግ ሉ፤ | ገጽ ፫፻፳፬ |
| አንቀጽ ፴፰.በእንተ ከመ መፍትው ናዕርፍ ሰን በታተ፤ | ገጽ ፫፻፳፯ | አንቀጽ ፴፰. በሰንበቶች ቀን ማረፍ እን ዲገባ፤ | ገጽ ፫፻፳፯ |
| አንቀጽ ፴፱. በእንተ ንዑሳ ክርስቲያን፤ | ገጽ ፫፻፴፫ | አንቀጽ ፴፱. ይጠመቁ ዘንድ ስለ ሚወለዱ ንዑስ ክርስቲያን፤ | ገጽ ፫፻፴፫ |
| አንቀጽ ፵. በእንተ ጸሎት ዘይትነበብ ዲበ ማይ፤ | ገጽ ፫፻፴፱ | አንቀጽ ፵. በክርስትና ጊዜ በመጠመቂያ ውሀ ላይ የሚጸ ለይ ጸሎት፤ | ገጽ ፫፻፴፱ |

## ማውጫ


| አንቀጽ | ገጽ | አንቀጽ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| አንቀጽ ፵፩. በእንተ ጸሎት ላዕለ ሜሮን። | ገጽ ፫፻፵፩ | አንቀጽ ፵፩. በሜሮን ላይ ስለ ሚጸለይ ጸሎት። | ገጽ ፫፻፵፩ |
| አንቀጽ ፵፪. በእንተ ዘከመ ይጸልዩ ዘንተ ጸሎተ ሐዲሳን እለ ተጠምቁ። | ገጽ ፫፻፵፩ | አንቀጽ ፵፪. አዲስ አማንያን ሲጠመቁ ስለሚጸልዩት ጸሎት | ገጽ ፫፻፵፩ |
| አንቀጽ ፵፫. በእንተ ኤጲስ ቆጳሳት እለ ተሠ ይሙ በነበ ሐዋ ርያት። | ገጽ ፫፻፵፪ | አንቀጽ ፵፫. በሐዋርያት ስለተሾሙ ኤጲስ ቆጳሳት የሚናገር። | ገጽ ፫፻፵፪ |

## አንቀጽ ፩

ዲድስቅልያ ዘውእቱ ትምህርት ዘአበው ቅዱሳን ሐዋርያት፤ ጸሎቶሙ ወበረከቶሙ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

በስመ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ወወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ወጸራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ።

፩ ንሕነ እሙንቱ ዐሠርቱ ወ፪ቱ ሐዋርያት ላእካኒሁ ለወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጋቢኦነ አሐተኔ በኢየሩሳሌም ሀገሩ ለንጉሥ ዐቢይ፤ ወምስሌነ እጉነ ጳውሎስ ጌር ወንጹሕ፤ ሐዋርያ ሆሙ ለኵሎሙ አሕዛብ፤ ወያዕቆብ እጉሁ ለእግዚእነ ዘውእቱ ኤጲስ ቆጶስ ለዛቲ ሀገር ኢየሩሳሌም ሠራዕናሃ ለዛቲ ርትዕት ትምህርት።

፪. ወአዘዝነ ከመዝ መዓርገ ሢመታት ለቤተ ክርስቲያን በአርአያ ዘበሰማያት።

፫. ወንሕነ ንጌሥጸክሙ ከመ ይንበር ኵሉ ለለ አሐዱ አሐዱ እምኔክሙ ውስተ ዘተጸውዐ እምኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

## አንቀጽ ፩

የቅዱሳን አበው ሐዋርያት ትምህርት ዲድስቅልያ፤ ጸሎታቸውና በረከታቸው ከእኛ ጋር ይኑር።

ሁሉን በያዘ በእግዚአብሔር አብ በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ናዛዚ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ ስም።

፩ የአንድያ ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች እኛ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በታላቁ ንጉሥ ከተማ በኢየሩሳሌም በአንድነት ተሰብስበን ከእኛም ጋር የአሕዛብ ሁሉ ሐዋርያቸው ደግና ንጹሕ ወንድማችን ጳውሎስ፤ የዚችው ከተማ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የጌታችን ወንድም ያዕቆብም ከእኛ ጋር ሆነው ይህችን የቀናች ትምህርት ሠራናት።

፪. የቤተ ክርስቲያንን የሹመቶች መዓርግ በሰማያት ባለው አምሳል እንደዚህ አዘዝን።

፫. ከእናንተም ሁሉ እያንዳንዱ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ በተጠራበት ጸንቶ ይኖር ዘንድ እኛ እንመክራችኋለን።

፬. ኤጲስቆጶስ በአምሳለ ኖላዊ፤ ወቀሳውስት በአምሳለ መገሥጻን፤ ወዲያቆናት በአርአያ ላእካን ፤ ወን ፍቀ ዲያቆናትሂ ናሁ ከመ ረዳእ ያን፤ ወአናጕንስጢሳውያን ከመ አንባብያን በጥይቅና፤ ወአብስሊ ድሳውያን ከመ መዘምራን፤ ወባ ዕዳንስ ከመ እለ ያጸምዑ ቃለ ወንጌል።

፭. ወዓዲ ይለብዉ ነገረ ተግ ሣጽ፤ እስመ ከመዝ ረከብነ ወሠ ራዕነ ሕገ ለቤተ ክርስቲያን ወጸሐፍነ ዘንተ መጽሐፈ ተግ ሣጽ ወፈነውነ ምስለ ቀሌምን ጦስ እጉነ ላእክ ለዝንቱ ዓለም ከመ ይሑሩ በትእዛዝ አብያተ ክርስቲያናት እለ መትሐተ ሰማይ ወይለብዉ ጥዩቀ ፤ ከመ ሶበ ሰምዑ ዘንተ ትእዛዘ ዘጽሑፍ ውስቴቱ፤ ወይርከቡ ሕይወተ ዘለ ዓለም ክብረ ወስብሐተ በጎበ እግ ዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጸገወነ ዘንተ ምሥጢረ ዘእምንቤሁ።

፮. ወእለ ኢየዐቅቡ ሕጎ ይወድቁ ውስተ እሳት ዘኢይጠፍእ፤ ወዓዲ ይከውን ምንባሮሙ ውስተ ገሃነም በከመ ጽሑፍ እስከ ለዓለም።[፩]

፩. ማቴ. ፳፭፤ ፵፩

፬. ኤጲስቆጶሱ እንደ ጠባቂ ነው፤ ቀሳውስትም እንደ መምህራን ናቸው፤ ዲያቆናትም እንደ አገልጋዮች ናቸው፤ ንፍቀ ዲያቆናትም እነሆ እንደ ረዳቶች ናቸው፤ አናጕንስጢሳውያንም በማስተዋል እንደ አንባብያን ናቸው፤ አብስሊድሳውያንም እንደ መዘምራን ናቸው፤ ሌሎች ግን የወንጌልን ቃል እንደሚያደምጡ ናቸው።

፭. ዳግመኛም የትምህርቱን ቃል ያስተውሉ፤ እንደዚህ ስላገኘነው ለቤተ ክርስቲያን ሕግ አድርገን ሠራን፤ ይህንም የምክር መጽሐፍ ጽፈን የዓለም መምህር በሆነው በወንድማችን በቀሌምን ጦስ እጅ ላክን፤ ከሰማይ በታች ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በትእዛዝ ፀንተው ይኖሩ ዘንድ፤ በውስጡ የተጻፈውንም ይህንን ትእዛዝ በሰሙ ጊዜ በእርግጥ ያስተውሉ ዘንድ፤ ይህንም ምሥጢር ከራሱ በሰጠን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የዘለዓለም ሕይወትን ኩሽርንና ምስጋናንም ያገኙ ዘንድ።

፮. ሕጉን የማይጠብቁ ግን በማ ይጠፉ እሳት ይወድቃሉ ፤ ዳግ መኛም እንደተጻፈ መኖሪያቸው እስከ ዘለዓለም ድረስ በገሃነም ውስጥ ይሆናል።

፮ ወሐዋርያትሰ ወቀሲሳን ወሶሎሙ አሕዛብ እለ አምኑ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወገብሩ ጽድቀ ወሰላመ ይረክቡ ሣህለ ወምሕረተ በኀበ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ዅሉ ዓለም ወወልዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወይበጽሑ ውስተ አእምሮ ዚኣሁ በቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ ለእግዚአብሔር ። ወእለሰ ተቀንዩ ሎቱ ይክውኑ ዐፀደ ወይን ንጹሐ ወጎሩየ ወይረ ክቡ ሕይወተ ዘለዓለም በዛቲ አሚን ወመዊእ በመንፈስ ቅዱስ። ወይጸንዑ በኀይለ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወበአሚነ ዚአሁ ዘቤዘዎሙ በንዝኅተ ደሙ ቅዱስ ወክቡር። ወጸገዎሙ ስብሐተ። ከመ ይጸውዕዎ ለኢኃዜ ዅሉ ከመ ይኩኖሙ አቡሆሙ ወአምላኮሙ ወዐር ኮሙ ወመዋርስቲሆሙ ወይረስዮሙ ሱታፌሁ ለወልድ ቅዱስ።

፯.ስምዑ ተግሣጸ ቅዱስ እለ ትትዌከፉ ቃለ ወንጌል በትእዛዘ መድኀኒነ ። ወዜናሁ ዘምሉዕ ስብሐተ አ ደቂቀ እግዚአብሔር ዕቀቡ ትእዛዛቲሁ ወግበሩ ሥም ረቶ።

፯. ነገር ግን ሐዋርያትና ቀሳውስት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያመኑ አሕዛብም ሁሉ ጽድቅንና ሰላምን ያደረጉም ሁሉን በያዘ በእግዚአብሔር አብና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅር ታንና ቸርነትን ያገኛሉ። በቅድስት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም እርሱን ወደ ማወቅ ይደርሳሉ። ለእርሱ ያገለገሉም ንጹሕና የተመረጠ የወይን ቦታ ይሆናሉ። በዚችም እምነት የዘለዓለምን ሕይወት ያገኛሉ። በመንፈስ ቅዱስም ድል መንሳትን ያገኛሉ። በኢየሱስ ክርስቶስም ኃይል ይጸናሉ። በቅዱስና ክቡር ደሙ ፈሳሽነት የዋጃቸው እርሱን ቦማመንም ይጸናሉ። አባታቸውና አምላካቸው ወዳጃቸውና ርስታቸው ይሆናቸው ዘንድ። የቅዱስ ልጁም ተባባሪዎች ያደርጋቸው ዘንድ ሁሉን የያዘውን እንዲጠሩ ክብር ሰጣቸው።

፰. በመድኀኒታችን ትእዛዝ የወንጌልን ቃል የምትቀበሉ ቅዱሱን ትምህርትና ክብርን የተመላውን ወንጌሉን ስሙ ። የእግዚአብሔር ልጆች ሆይ! ትእዛዙቱን ጠብቁ። ፈቃዱንም አድርጉ።

፱. ወእመሰ ቦ ዘየኀሥሥ ይት ልዋ ለኀጢአት ወይገብር ኵሎ ዘኢያሠምሮ ለእግዚአብሔር ፤ ውእቱኬ ይትኤለቍ ምስለ እለ ዐለዉ ሕጎ ወትእዛዞ።

፲ ወይእዜኒ እብለክሙ ፤ ረኀቁ እምዐመፃ ወትዕግልት ፤ ወኢት ፍቅዱ ለርእስክሙ ነሢአ ክፍል ዘየዐቢ ፤ ወለቢጽክሙ ኀዳጠ ፤ እስመ ጽሑፍ ውስተ ሕግ ዘይብል «ኢትፍቱ ብእሲተ ካል እከ ኢገራህቶ ወኢገብሮ ወኢ አመቶ ኢላሕሞ ወኢአድኅ ወኢ ምንተኒ ኵሎ ንዋዮ ለእጉከ»[፪] ወከሉ ዘይመስሎ ለዝንቱ ዝሙት ውእቱ።

፲፩. ወእመሰ ቦ ዘይፈቅድ ይግ በር ከመዝ በፍትወተ ልቡ ይከውን ርኁቀ እምእግዚእነ ኢየ ሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ዘለዓለሙ ስብሐት ምስለ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፲፪.እስመይሜህረነ፤ ወያሌብወነ፤ ወያጸንዐነ በመንፈስ ቅዱስ ከመ ንፈጽም ሕገ ዘጽሑፍ ውስቴቱ፤ ዘይብል ኢትዘምዉ።

፪. ዘፀ. ፳ ፡ ፲፯

፱. ኀጢአትን ይከተል ዘንድ የሚ ፈልግ፤እግዚአብሔርንም ደስ የማ ያሰኘውን ሁሉ የሚሠራ ቢኖር ግን እርሱ ሕጉንና ትእዛዙን ከለ ወጡ ሰዎች ጋር ይቈጠራል።

፲.አሁንም እላችኋለሁ፤ ከዐመፅና ከቅሚያ ራቁ፤ ለራሳችሁ የሚበል ጠውን ክፍል መውሰድን፤ለወን ድሞቻችሁ ግን ጥቂት መስጠ ትን አትውደዱ፤ በሕግ እንዲህ የሚል ተጽፎአልና « የባልንጀራ ህን ሚስቱን፤ እርሻውን፤ ወንድ ባሪያውን ፤ ሴት ባሪያውን፤ በሬ ውንም፤ አህያውንም ፤ ማንኛው ንም የወንድምህን ገንዘብ ሁሉ ምንም አትመኝ» ይህንም የመ ሰለው ሁሉ ዝሙት ነው።

፲፩. በልቡ ምኞት እንደዚህ ይሠራ ዘንድ የሚወድ ቢኖር ግን ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለዘለዓለም ክብር ምስጋና ከሚገባው ከጌታችን ከእግዚአብሔር ኢየሱስ ክር ስቶስ የራቀ ይሆናል አሜን።

፲፪. በመንፈስ ቅዱስ ያስተምረ ናልና እንድናውቅም ያደርገናልና፤ ያጸናናልና አትሰንፉ የሚል በውስጡ የተጻፈበትንም ሕግ እንፈጽም ዘንድ።

፲፫.« ወአንሰ እብለክሙ ኵሉ ዘር እያ ለብእሲት ወፈተዋ ወድአ ዘመወ ባቲ በልቡ[፫]» ::

፲፬.ወዓዲ ዘይፈቅድ ይግበር ከመዝ ይትኬነን ምስለ ዘማውያን::

፲፭. ወናሁ ከመ ውእቱ ዘይኄሊ በልቡ ወይፈቱ ይንሣእ በዐመፃ ላህሞ፤አው አድጎ፤ አው ገራህቶ፤ ወያሐዩ እንዘ ከመዝ ይገብር ይትኄለቍ ምስለ ዘማውያን እስመ ይቤ በነቢይ አሌ ሎሙ ለእለ ያስተአዝዙ ቤተ ምስለ ቤት፤ ወለእለ ያስተቃርቡ ገራህተ ምስለ ገራህት፤ ወጥቅመ ምስለ ጥቅም ከመ ይሂዱ ዘኢኮነ ዚአሆሙ፤[፬]

፲፮. ወካዕበ ይቤ አእምሩ አንትሙ እለ ትነብሩ ዲበ ምድር ከመ ትስምዑ ዘንተ ነገረ ከመ በጽሐ ነገርክሙ ውስተ እዘኒሁ ለእግዚአ ብሔር ጸባኦት:: በውስተ ካልዕኒ ይብል «ርጉመ ለይኩን ኵሉ ዘይ ሰርቅ ደወለ ቢጹ ወይበል ሕዝብ ለይኩን፤ ወበእንተዝ፤ ይብል

፲፯.እኔ ግን ሴትን አይቶ የተመኛ ት ሁሉ ፈጽሞ አመነዘረባት ብዬ እነግራችኋለሁ::

፲፰. ዳግመኛም እንደዚህ ይሠራ ዘንድ የሚወድ ሰው ከዘማውያን ጋራ ይፈረድበታል::

፲፱. እነሆ በሬውን ወይም አህያ ውን ወይም እርሻውን በግፍ ይቀማ ዘንድ በልቡ የሚያስብና የሚመኝ እንዲህም እያደረገ የሚኖር ከዘማውያን ጋራ ይቈ ጠራል፤የራሳቸው ያልሆነውን ይቀሙ ዘንድ ቤትን ከቤት ጋራ ለሚያያይዙ ፤ እርሻንም ከእርሻ ጋር፤ ለሚያቀራርቡ ቅጥርንም ከቅጥር ጋር ለሚያቀራርቡ ወዮ ላቸው ተብሎ በነቢይ ተነግሮ አልና::

፳.ዳግመኛም እንዲህ አለ፤ በምድር ላይ የምትኖሩ እናንተ ሆይ፤ ነገራ ችሁ ወደ ሠራዊት ጌታ ወደ እግ ዚአብሔር ጆሮዎች እንደ ደረሰ ይህን ነገር ትሰሙ ዘንድ ዕወቁ፤ በሌላም ክፍል ውስጥ የወንድሙን ድንበር የሚሰርቅ ርጉም ይሁን፤ ሕዝቡም ይሁን (አሜን) ይበል

---

፫. ማቴ. ፭ ፡ ፳፰

፬ አሊ. ፭ ፡ ፫ ፤ ዘጣ. ፳፯ ፡ ፲፯

ሙሴ «ኢትፍቱ ደወለ ካልእከ ወኢትንስት ሕገ ዘሠርዐ አበ ዊከ»[፩]

፲፯. ወእንበይነዝ ይብል ይከ ውን ፍርሀት፤ ወሞት፤ ወሀከክ፤ ወይረክቦሙ ኵነኔ እንተ እምኀበ እግዚአብሔር ለእለ ይገብሩ ከመዝ።

፲፰ ወሰብእሰ እለ ያጸምዑ ቃለ እግዚአብሔር ፤ ወየዐቅቡ ሕጎ ብሩህ በአማን ይረክቡ ሣህለ ወምሕረተ፤ እስመ ይቤ ዘትጸልእ ለርእስከ ኢትግበር ዲበ ቢጽከ[፪]፤ ወበከመ ኢትፈቅድ አንተ ይርአይ ባዕድ ብእሲተከ ወኢመኑሂ ከመ ያስሕታ በእከይ፤ ወከማሁ አንተኒ ኢትነጽር ብእሲተ ባዕድ በእኩይ ሕሊና፤ ወበከመ ኢትፈቅድ ይን ሣእ ልብሰከ ካልእ ከማሁ አንተሂ ኢትንሣእ ልብሰ ባዕድ፤ ወበከመ ኢትፈቅድ ለርእስከ መርገመ ወፅዕለተ፤ ወዝብጠተ፤ ከማሁ አን ተኒ ኢትግበር በካልእከ።

ሙሴም ስለዚህ ነገር እንዲህ ይላል «የወንድምህን ድንበር አትሻ አባቶችህም የሠሩትን ሕግ አታፍርስ»።

፲፯. ስለዚህም ነገር ፍርሀት ሞትና ክርክር ይሆናል፤ እንደዚህም የሚያደርጉትን ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣት ያገኛቸዋል።

፲፰. የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ብሩህ ሕጉን የሚጠብቁ ሰዎች ግን ይቅርታንና ምሕረትን ያገኛሉ ፤ ለራስህ የምትጠላውን በባልንጀራህ ላይ አታድርግ ብሏልና፤ አንተ ሌላው ሰው ሚስትህን ያይ ዘንድ ማንም በተንኰል ያስታት ዘንድ እንደማትወድ እንደዚሁ አንተም የሌላውን ሚስት በክፉ ሕሊና አታስብ፤ ሌላውም ልብስህን ይወስድብህ ዘንድ እንደ ማትወድ እንደዚሁ አንተም የሌላውን ልብስ አትውሰድ፤ ለራስህም መርገምን ስድብንና መመታትን እንደማትወድ እንደዚሁ አንተም በሌላው አታድርግ።

---

፩. ዘዳግ. ፲፱ ÷ ፲፯

፪ ማቴ. ፯ ÷ ፲፪

፲፱. ወለእመቦ ዘረገመከ ወአንተሰ ባርክ እስመ ጽሑፍ ዘይብል ውስተ መጽሐፈ ጕልቍ «እለ ይባርኩከ ቡሩካነ ለይኩኑ፤ ወእለ ይረግሙከ ርጉማነ ለይኩኑ»[፮] ::

፳. ወዓዲ ጽሑፍ ውስተ ወንጌል «ደኅርዎሙ ለእለ ይረግሙክሙ ወጸልዩ ዲበ እለ ይትዔገሉክሙ አላ ተዐገሥዎሙ፤ ወግበሩ ሠናየ ለእለ ይጸልኡክሙ ወኢትፍድዩ እኩየ ለእለ ይትዔገሉክሙ አላ ተዐገሥዎሙ»[፯] ፤ እስመ ይብል መጽሐፍ ኢትትበቀል ጸላኤክ ሀየ ንተ ዘገብረ ለክ እኩየ::[፱]

፳፩. ወበእንተዝ ይረድእከ እግዚ አብሔር ወያገብእ ሎኅኔ ላዕለ ጸላኢክ እስመ ይብል በወንጌል «አፍቅሩ ጸላዕተክሙ ወጸልዩ በእ ንተ እለ ይሰድዱክሙ ከመ ትኩኑ ውሉዶ ለአቡክሙ ዘበሰማያት እስመ ውእቱ ያሠርቅ ፀሐየ ላዕለ እኩያን ወኄራን ወያዘንም ዝናመ ላዕለ ጻድቃን ወዐማፅያን»[፲] ::

፳፪.አ ፍቁራኒነ ንለቡ እሎንተ ትእ ዛዛተ ከመ ንኩን ውሉደ ብርሃን ወተዐገሡ በበይናቲክሙ አ ውሉደ እግዚአብሔር ::

---

፮. ዘኍል. ፳፬ ፤፳
፯. ሉቃ ፮ ፤ ፳፯-፳፱
፱. ምሳ. ፳ ፡ ፳፪
፲. ማቴ ፭ ፵፬ - ፵፭

፲፱. የረገመህም ቢኖር አንተ መርቅ፤ በኦሪት ዘጕልቍ «የሚ መርቁህ የተመረቁ ይሁኑ፤ የሚ ረግሙህም የተረገሙ ይሁኑ» የሚል ጽሑፍ አለና::

፳. ዳግመኛም በወንጌል እንዲህ ተጽፎአል«የሚረግሙአችሁን መር ቋቸው፤ ለሚቀሟቸሁም ጸልዩ ፤ ለሚጠሉአችሁም በጎ ሥራን አድ ርጉ፤ ለሚቀሙአችሁም ክፉ አት መልሱ» «ነገር ግን ታገሡአቸው፤ መጽሐፍ እንዲህ ይላልና «ክፉ ስለ አደረገብህ ጠላትህን አት በቀል» ይላልና::

፳፩. ስለዚህም ነገር እግዚአብሔር ይረዳሃል፤ፍርድንም በጠላትህ ላይ ይመልሳል፤ በወንጌል እንዲህ ብሏልና «የሰማያዊ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻች ሁን ውደዱ ፤ ስለሚያሳድዷች ሁም ጸልዩ፤ እርሱ ለክፉዎችም፤ ለበጎችም ፀሐይን ያወጣልና፤ ለጻድቃንም ለኃጥአንም ዝናምን ያዘንማል ብሏልና::

፳፪. ወዳጆቻችን ሆይ፤ የብርሃን ልጆች እንሆን ዘንድ እነዚህን ትእ ዛዛት እናስተውል፤የእግዚአብሔር ልጆች ሆይ ፤ እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን ያዙ::

፳፫. ወብእሲኒ ይትዐገሣ ለብእ ሲቱ፤ ወኢይኩን ዕቡየ ወመደ ልወ አላ ይኩን መሓሬ ወራትዐ ወያሠንያ፤ ለባሕቲታ በፍቅር ወበ ትሕትና ኢየአድም ወኢይፍቱ ካልእተ ብእሲተ ከመ ኢታስሕቶ።

፳፬. ወእመሰ ዘመውከ ወገበርከ ከመዝ መዊተ ትመውት፤ ወይ መጽእ ላዕሌከ መቅሠፍት እም ኀበ እግዚአብሔር፤ ወትትኴነን መሪረ ሞኔ፤ ወባሕቱ እመ ኀለ ይከ በልብከ ወዘመውከ ምስሌሃ ይከውነከ ኀጢአተ።

፳፭. ወእመሂ ተደለውከ ወተሠ ነይከ ከመ ታፍቅርከ ብእሲተ ካልእከ ጊገይከ ወኮንከ ላቲ ዕቅ ፍተ ወአዘመውካ፤ ወበእንተዝ ይመጽእ ላዕሌከ ሞኔ፤ እስመ ይቤ እግዚአብሔር ኢትፍቱ ወኢ ትዘሙ፤ እስመ እስሐትካ በስነ ውርዙትከ ወላህየ ገጽከ ከመ ታፍቅርከ፤ ወበእንተ ዝ ተሳተፍከ ምስሌሃ ኀቡረ ውስተ ግብረ ኀጢአት ወመርገም።

፳፫. ወንድ ሚስቱን ይታገሣት፤ ትዕቢተኛና ግብዝም አይሁን፤ ነገር ግን የሚራራና ቅን ይሁን፤ ለብቻዋም በፍቅርና በትሕትና ደስ ያሰኛት፤ እንዳታስተውም ሌላዪቱን ሴት አይውደድ፤ አይመኛትም።

፳፬. ብትሰስን እንደዚህም ብታደ ርግ ግን ሞትን ትሞታለህ፤ ከእግ ዚአብሔር ዘንድም መቅሠፍት ባንተ ላይ ይመጣል፤ መራራ ፍር ድም ይፈረድብሃል ፤ ነገር ግን በልብህ አስበህ ከእርሷ ጋራ ብት ሰስን ኀጢአት ይሆንብሃል።

፳፭. የባልንጀራህም ሚስት ትወ ድህ ዘንድ ብትዘጋጅና ብታጌጥ ከደልህ ፤ ለእርሷም መሰናክል ሆንህ ፤ አሰስንካትም፤ ስለዚህም ነገር ባንተ ላይ ፍዳ ይመጣል፤ እግዚአብሔር አትሰስን ፤ አትመ ኝም ብሏልና፤ ትወድህ ዘንድ በጕልማሳነትህ መልክና በፊትህ ደምግባት አስተሃታልና፤ስለዚህም በኃጢአትና በርግማን ሥራ ከርሷ ጋራ ተባበርክ ።

፭፮. ወበእንተዝ ይደልወከ ከመ ትስአሎ ለእግዚአብሔር አምላ ክከ ከመ ኢይርከብከ ዝንቱ ኵሉ ኀጢአት፤ ወባሕቱ አንተሰ መፍ ትው በንጽሕ ታሥምሮ ለእግ ዚአብሔር ከመ ትርከብ ዕረፍተ ወሕይወተ ዘለዓለም· በኀበ እግዚ አብሔር፤ እስመ ይቤ ኢታንኀ ሥዕርተ ርእስከ አላ ዳዕሙ ቅርጽ ወአንጽሕ ርእስከ ከመ ትትቀነይ ለእግዚአብሔር ወኢትትፈለጥ እምኔሁ።

፭፯. ወአንተሰ ኢትትቀባዕ ቅብዓ መዐዛ ወኢትልበስ አልባሰ ሠርጉ ለአስሕቶ አንስት ፤ ወኢትትመ ካሕ ወኢትኩን ማዕቅፈ አላ ኀሥሥ ንጽሐ ወገቢረ ሠናይ።

፭፰. ወአንተሰ አ ብእሴ እግዚአ ብሔር ኢታንኀ ሥዕርተ ርእስከ ኢትፍትል ወኢትጽፍሮ እስመ ዝንቱ ኵሉ ትእምርተ ርኵስ ወዝሙት ውእቱ ፤ እስመ ጽሑፍ ውስተ ዳግም ሕግ ወኢ ትልበስ ልብሰ ዘተአንመ በፀምር ወበአሴ፤ ወኢትግበር ለከ ዘፈረ ፍቱለ በልብስከ[፲፩]።

፭፱. ስለዚህም ይህ ሁሉ ኃጢአት እንዳያገኝህ እግዚአብሔርን ትሰ ምነው ዘንድ ይገባሃል፤ ነገር ግን አንተ በእግዚአብሔር ዘንድ ለዘ ለዓለም ሕይወትንና ዕረፍትን እን ድታገኝ በንጽሕና እግዚአብሔርን ደስ ታሰኘው ዘንድ ይገባል ፤ ለእግ ዚአብሔር ትገዛ ዘንድ ከርሱም እንዳትለይ የራስህን ጠጉር አታሳ ድግ፤ ጠጉርህን ቊረጥ፤ ራስ ህንም ንጹሕ አድርግ ብሏልና።

፷. አንተ ግን ሽቱ ያለበትን ዘይት አትቀባ ፤ ሴቶችንም ለማ ሳት የጌጥ ልብስ አትልበስ ፤ አትመካ ፤ መሰናክልም አትሁን፤ ነገር ግን ንጽሕናንና በጎ ሥራ መሥራትን ፈልግ ።

፷፩. አንተ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ፤ የራስህን ጠጉር አታሳ ድግ፤ ሥሉስ አትሠራ፤ ሹርባ አትሠራ፤ ይህ ሁሉ የርኵሰትና የዝሙት ኃጢአት ምልክት ነውና፤ በአሪት ዘዳግም ከበግ ጠጉር ብዝት፤ ከተልባ እግር በሐር ጥጥ የተሠራ ልብስን አትልበስ የሚል፤ ጽሑፍ አለና ለልብስህም የተፈተለ ዘርፍን አታደርግለት።

---

፲፩. ዘዳግ፤ ፳፪ - ፲፩

፸፱.ወባሕቱ ኢመፍትው ለነ ንላዒ ጽሕመነ፤ ወኢንወልጥ ፍጥረተ ብእሲ ውስተ ካልዕ ግዕዝ፤ ወእመሰ ትገብር ከመዝ ኮንከ ውጹአ እምሕግ ፤ ወርኁቀ እምእግዚ አብሔር ዘፈጠረከ በአርአያሁ ወበ አምሳሊሁ።

፹. ወእመሰ ትፈቅድ ታሥምሮ ለእግዚአብሔር ኢትግበር እኩየ ወአርኁቅ እምኔከ ኵሎ ዘይጸልእ አምላክከ፤ ወኢትኩን ለካሬ፤ ወኢ ታንሶሱ ውስተ መራኁብት ምስለ ዘማውያን ዘእንበለ ጥበብ ወአ እምሮ፤ አላ አንተሰ ተቀነይ ወሕየው ቦንብረ እደዊከ ወነሥሥ ትግበር ኵሎ ዘያሠምሮ ለእግ ዚአብሔር ወተዘከር ቃሎ ለእግ ዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወትሉ ኪያሁ ኵሎ ጊዜ ።

፹፩. እስመ ይብል ዳዊት «ወዘ ሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ[፲፪]፤ ወእመሂ በፍናት፤አው በውስተ ቤት፤ ወእመሂ እንዘ ትነውም አፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ሕሊናከ ወበኵሉ ኀይልከ ከመ ትርከብ በኀቤሁ ሣህለ ወምሕረተ።[፲፫]

፸፱. ነገር ግን ጽሕማችንን እን ላጭ ዘንድ ለኛ አይገባንም፤ የሰ ውንም ተፈጥሮ ወደ ሌላ ባሕርይ አንለውጥ፤ እንዲህ ካደረግህ ግን ከሕግ የወጣህ ሆንህ ፤ በአርአ ያውና በአምሳሉ ከፈጠረህ እግዚ አብሔርም የተለየህ ሆንህ።

፹. እግዚአብሔርን ደስ ታሰኘው ዘንድ ከወደድህስ ክፉ ሥራን አት ሥራ፤ ፈጣሪህም የሚጠላውን ሁሉ ከአንተ አርቅ፤ ለካራም አትሁን፤ ከዘማውያንም ጋራ በአደባባይ አት ዙር፤ አእምሮ ጠባይዓዊን አእምሮ መንፈሳዊን ያዘ እንጂ ፤ አንተ ግን በእጆችህ ሥራ ጥረህ ግረህ ተመገብ እንጂ፤ እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኘውን ሥራ ሁሉ ትሠራ ዘንድ ውደድ፤ ሁልጊዜም እሱን ትከተል ዘንድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃሉን አስብ።

፹፩. ዳዊት በመዓልትም በሌሊ ትም ሕጉን የሚያነብ ብፁዕ ነው ብሏልና፤ በጉዳናም ቢሆን ፤ በቤ ትም ቢሆን፤ ስትተኛም ቢሆን፤ ከእርሱ ይቅርታንና ቸርነትን ታገኝ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን በፍ ጹምሕሊናህ፤ በፍጹም ልቡናህ፤ በፍጹም አእምሮህ ውደደው።

---

፲፪. መዝ. ፩ ፡ ፪

፲፫. ዘዳግ. ፮ ÷ ፭ - ፮

## አንቀጽ ፪

በእንተ ከመ መፍትው ለአብ ዕልት ይኅሥሡ አእምሮ ረባሕ እመጻሕፍት በኀይለ መንፈስ ቅዱስ ዘሎ ጊዜ ::

፩. ወእመሰ ባዕል አንተ ወኢት ፈቅድ ኪነ ወቅኔ እድ በዘትሴ ሰይ ወተሐዩ ቦቱ ኢትትሀከይ ወኢትንበር ጽሩዐ፤አላ ሑር ኀበ መሃይምናን ወንበር ምስለ እለ የኀብሩ ምስሌከ ሃይማኖተ፤ወተ ናገር ነገረ ሕይወት፤ ወአንብብ ዘውስተ መጽሐፈ ነገሥት፤ወነ ቢያት፤ ወዘምር መዝሙረ ስብ ሐት፤ ወአጽምዕ ቃለ ወንጌል ዘውእቱ ተፍጻሜተ ዘሎ ሕግ::

፪. ወረኀቅ እምዘሎ ቅኔ ዘአማ ልክተ አሕዛብ፤ ወኢያጽሕቀ ዘሎ ነገረ ከንቱ ዘኢይበቍዕ፤ ወኢት ኅሥሥ ካልአ ሕገ ወሐሳውያን ነቢያት እለ ይዌልጡ ወያማስኑ ሃይማኖተ፤ ምንተ እንከ ለእንከ እምውስተ ሕገ እግዚአብሔር ከመ ትሕሥሥ ትምህርተ አሕ ዛብ ::

## ሁለተኛ አንቀጽ

በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ከመጻሕ ፍት የተገኘውን ጥቅም ማወቅን ሁለ ጊዜ ይመረምሩ ዘንድ ለባለ ጸጋች እንደሚገባ ይናገራል።

፩. አንተ ባለጸጋ ብትሆን እንድ ትመገብና በሕይወት እንድትኖር ጥበብንና ተግባረ እድን ባትሻም ለነፍ አትሁን፤ሥራ ፈት ሆነህም አትኑር፤ነገር ግን ወደ ምእመናን ሄደህ በሃይማኖት ከአንተ ጋር ከሚተባበሩ ጋር አብረህ ኑር፤ የሕይወትንም ነገር ተናገር፤ በነገ ሥትና በነቢያት መጽሐፍ ውስጥ ያለውንም ተመልከት፤ የምስጋና መዝሙርን ዘምር፤ የሕግ ሁሉ ፍጻሜ የሚሆን የወንጌልንም ቃል ስማ ::

፪. ከአሕዛብ አማልክት መገዛት ሁሉ ራቅ፤ ለማይረባ ለማይጠ ቅም ለከንቱ ነገር ሁሉ አት ጨነቅ፤ ከወንጌል ልዩ የሚሆን ሕግንና ሃይማኖትን ለውጠው የሚያጠፉ ሐሰተኞች መምህራ ንን አትሻ፤የአሕዛብን ትምህርት ትሻ ዘንድ ከእግዚአብሔር ሕግ ከኦሪት፤ ከወንጌል ምን አጣህ?

፫. ወእመሰ ትፈቅድ ታእምር አንብቦ ኀይለ ትርጓሜ መጻሕፍት ኅሥሥ መጽሐፈ ነገሥት፤ ወእመሂ ጽሕቀ ትጠይቅ ኀበ ጠቢባን ወትምህርቶሙ ለነቢያት ብክ ኢዮብ ወሰሎሞን፣ እሉ እሙንቱ ምሉአነ ጥበብ፤ ወትረክብ በኀቤሆሙ አእምሮ እለ ያፈደፍዱ ለብዎ እምኵሉ መምህራን፤ እስመ ነገሮሙ ቃለ እግዚአብሔር አምላክ ዘውእቱ ባሕቲቱ ጠቢበ ጠቢባን ወእመሰ ትፈቅድ ማኅሌተ ብክ መዝሙረ ዳዊት፤ ወእመሂ ተኀሥሥ ትለቡ ፍጥረተ ዓለም ወልደተ አዝው ቀደምት ብክ አሪት፤ ወእመኒ ትፈቅድ ታእምር ጥበበ ወትምህርተ ብክ መጽሐፈ ሕግ ዘምሉእ ውስቴቱ ስብሐተ እግዚአብሔር አምላክ።

፬. ረኃቅ እንክ እምግብር እኩይ ወትምህርተ ሰይጣን ወነገረ ከንቱ ዘኢሀለዉ ውስተ ሕግ፤ አላ አንብብ ውስተ ዳግም ሕግ ከመ ትለቡ ወትጠይቅ ስብሐቶ ለእግዚአብሔር ዘአድኀነከ እምብዙኅ መሣግሪሁ ለሰይጣን፤ እስመ ኢመጽአ መድኀን ከመ ይንሥቶሙ ለአሪት ወለነቢያት አላ ከመ

፫. የመጻሕፍትን ትርጓሜ መመልከትንስ ታውቅ ዘንድ ብትወድ የነገሥትን መጽሐፍ ተመልከት፤ የመተርጕማንን ዕውቀት፣ ትምህርታቸውንም ትረዳ ዘንድ ብትተጋ ኢዮብ፤ ሰሎሞን አሉልህ፤ እሊህም ጥበብን የተመሉ ናቸው፤ ከመምህራን ሁሉ ዕውቀትን ከሚያበዙ ከእነርሱ ዕውቀትን ታገኛለህ፤ ነገራቸው ብቻውን የአዋቂዎች አዋቂ የሚሆን የፈጣሪ የእግዚአብሔር ቃል ነውና፤ ማኅሌትንስ ከወደድህ የዳዊት መዝሙር አለልህ፤ ሥነ ፍጥረትን የቀደሙ አበውንም ልደት ብትሻ አሪት አለልህ፤ ትምህርትና ጥበብን ልታውቅ ብትወድ በውስጡ የፈጣሪ የእግዚአብሔር ጌትነት የተመላበት የሕግ መጽሐፍ አለልህ።

፬. እንግዲህ በሕግ ከሌሉ ከክፉ ሥራ ከሰይጣን ትምህርትና ከከንቱ ነገር ራቅ፤ ነገር ግን ከብዙ የሰይጣን ወጥመድ ያዳነህን የእግዚአብሔርን ጌትነት ታስተውልና ትረዳ ዘንድ ዳግም ሕግን አንብብ፤ አሪትን ነቢያትን ያሳልፋቸው ዘንድ

ይፈጽሞሙ[፩] ወይፍታሕ ማእ
ሠረ ዘውስተ ዳግም ሕግ ወያግ
ብኦሙ ውስተ ትምህርት መንፈ
ሳዊት፤ ወበእንተዝ ይጼውዕነ
እንዘ ይብል ንዑ ኀቤየ ኵልክሙ
ጽዑራን ወክቡዳነ ያር ወእነ
አዐርፈክሙ።። [፪]

፫. ወአንተሰ እምከመ አንበብከ
አሪተ፤ ወነቢያተ፤ ወነገሥተ፤
ወወንጌለ ትሴቡ ሚመጠን ዕደው
ጻድቃን እለ ነግሡ ወአሥመርዎ
ለእግዚአብሔር በሕይወቶሙ፤ ወበ
እንተዝ ረከቡ ሕይወተ ዘለዓለም፤
ወዓዲ ተአምር ስፍነ ነገሥተ
ርዙሳነ እለ ዐዚዉ በኢለብዎቶሙ፤
ወእሙንቱሰ ማለኑ ወጠፍኡ በመ
ቅሠፍተ መዓቱ፤ ተኰነኑ ወኀ
ጕሉ ሕይወተ ዘለዓለም፤ ወእመ
ጠየቀ ዘንተ ትጸንዕ በርትዕት
ሃይማኖት፤ ወትረክብ ጸጋ ወሞገሰ
በኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ
እስመ ኮንከ ሎቱ አባለ።

፮. ወአንተሰ ሶበ ትፈቅድ ትት
ሐፀብ ኢትባእ ውስተ ቤተ ብለኔ
ኀበ ይትሐፀባ እንስት፤ ከመ ኢይር
አያ ሥነ ውርዙትከ ወላህየ ሥጋከ፤
ወኢይትዐቀፋ ብከ ወለሊከኒ ኢተ
አብስ፤ ወኢትድኀፅ ቦቶን ።።

፩. ማቴ ፭ ፡ ፲፯
፪. ማቴ ፲፩ ፡ ፳፰

አልመጣምና በዳግም ሕግ የነበረ
ውን እስራት ይፈታ ዘንድ ወደ
መንፈሳዊ ትምህርት ወደ ወንጌ
ልም ይመልሳቸውና ይፈጽማ
ቸው ዘንድ ነው እንጂ፤ ስለዚ
ህም እናንት ደካሞች ሸክማችሁ
የከበደ ሁላችሁ ወደኔ ኑ፤ እኔም
አሳርፋችኋለሁ እያለ ይጠራናልና።።

፫. አንተስ አሪትን፤ ነቢያትን፤ ነገ
ሥትን፤ ወንጌልንም የተመለከትህ
እንደሆነ በሕይወተ ሥጋቸው ነግ
ሠው እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙት
ጻድቃን ሰዎች ምን ያህል እን
ደሆኑ ታውቃለህ፤ ስለዚህም የዘለ
ዓለም ሕይወትን አገኙ፤ ዳግመ
ኛም ባለ ማወቃቸው የካዱ ርኩ
ሳን ነገሥታት ስንት እንደ ሆኑ
ታውቃለህ፤ እነርሱም በቀጣው
መቅሠፍት ፍርድ ፈጽመው ጠፉ፤
የዘለዓለም ሕይወትንም አጡ ፤
ይህንንም ብትረዳ በቀናች ሃይ
ማኖት ትጸናለህ፤ ከጌታችን ከኢየ
ሱስ ክርስቶስ ዘንድም ባለሟል
ነትን ታገኛለህ ፤ ለእርሱ አካል
ሁነሃልና።።

፮. አንተ ግን ትታጠብ ዘንድ በወ
ደድህ ጊዜ የሕፃንነትህን ደም ግባ
ትና የሰውነትህን ማማር እንዳ
ያዩ በአንተም እንዳይሰናከሉ፤ አን
ተም እንዳትበድል፤ በእነርሱም እን
ዳትሰነካከል፤ ቤቶች ወደሚታጠ
ቡበት መታጠቢያ ቤት አትግባ።

፭. ንስማዕ ወንለቡ ቃለ ቅዱሰ ዘይቤ መጽሐፈ ምሳሌ «ወልድየ ዕቀብ ነገረ ዚአየ፤ ወትእዛዘ ዚአየ ኅባዕ ኀቤከ»።

፮. ወበላ ለጥበብ እኅተ ዚኣየ አንቲ፤ ወለአእምሮ ሀገሪተከ ረስያ።

፱. ከመ ትዕቀብከ እምብእሲት ነኪርት ወእኪት አመ ነገረ ዘርቅ አምጽአት ለከ ።

፲. እስመ እመስኮተ ቤታ ውስተ መራሕብት ትሔውጽ።

፲፩. ዘርእየት እምአብዳን ውሉድ ወሬዛ ነዳየ አእምሮ።

፲፪. ዘየሐውር በፍናወ ማእዘንተ ቤታ ወይትናገር።

፲፫. በጽልመት ሠርከ ሶበ ይከ ውን ጽማዌ ወጽልመተ ሌሊት።

፲፬. ወሶቤሃ ትዳደቆ ብእሲት እንተ ባቲ ትርሲተ ዝሙት፤ እንተ ትሬሲ ይሥርር ልበ ወራዙት።

፲፭. ሥርርትይእቲ ፤ ወምርዕት፤ ወበቤታኒ ኢየዐርፉ እገሪሃ ።

፲፮. ወምዕረ ጎዳጠ ታንጐጉ አፍኣ፤ ወምዕረ ጎዳጠ ውስተ መራሕብት፤ ወውስተ ኵሉ ማእዘንት ትጸንሕ።

፭. መጽሐፈ ምሳሌ የሚለውን ቅዱስ ቃል ሰምተን እናስተውል፤ «ልጄ ሆይ!ቃሌን ጠብቅ፤ ትእዛዜንም በአንተ ሸሽግ።

፮.ጥበብን አንቺ እኅቴ ነሽ በላት፤ ማስተዋልንም ወዳጅ አድርጋት፤

፱. ክፋዕድና ከክፉ ሴት ዋዛ፤ ነገርንም ከምታመጣብህ ትጠብቅህ ዘንድ።

፲. በቤቷ መስኮት ሆና ወደ ዐደባባይ ትመለከታለችና።

፲፩. ከአላዋቂዎች ወጣቶች መካከል ከዕውቀት ድሃ የሆነውን ጉል ማሳ ብታይ።

፲፪. በቤትዋም አቅራቢያ ባለው መንገድ ሲሄድ ሲናገርም።

፲፫. ማታ ሲመሽ ውድቅትም ሲሆን በሌሊት በጽኑ ጨለማ።

፲፬. የምንዝር ጌጥ ያላት የጉል ማሶችን ልብ እንዲሰቀል የምታደርግ ሴት ያን ጊዜ ትገናኘዋለች።

፲፭. እርስዋ የምትበርር፤ መዳራትንም የምትወድ ናት፤ በቤትዋም እግሮቿ አያርፉም ።

፲፮. አንድ ጊዜ በጉዳና፤ በሌላ ጊዜም በዐደባባይ፤ በማእዘኑም ሁሉ ታደባለች።

፲፯. አጎዘቶ ወሰዐመቶ ወዘእን በለ ጎፍረት ትቤሎ በገጽ።

፲፰. መሥዋዕተ ሰላምየ ውእቱ፤ ዮም ብፅዐትየ እሁብ።

፲፱. በእንተ ዝንቱ መጻእኩ እት ቀበልከ፤ ወእንዘ አፈቅር ገጸ ዚአከ ረከብኩከ ።

፳. በቀጠንት ገለድኩ ምስካብየ፤ ወዘርቤታተ ነጸፍኩ ዘእምግብፅ።

፳፩. ነስነስኩ ምስካብየ መጽርየ፤ ወቤትየኒ በቀናንሞስ ።

፳፪. ነዓ ናስተሐውዝ በተላዕሞ እስከ ነግህ ፤ ወናንገርግር በተፋቅሮ።

፳፫ እስመ ኢሀሎ ምትየ ውስተ ቤቱ፤ ወሖረ ፍኖተ ርኁቀ፤

፳፬. ነሚአ ውስተ እዴሁ ዕቍረ ወርቅ፤ በመዋዕል ብዙኀ እመ ገብአ ውስተ ቤቱ።

፳፭. ወአስሐተቶ በብዙኀ ነገር፤ ወበመሥገርተ ከናፍር ሰሐበቶ።

፳፮. ወተለዋ ደኒኖ ከመ ላሕም ዘየሐውር ለተጠብሖ፤ ወከመ ከልብ ለተአሥር[፫] ።

፳፯. ወዓዲ ይቤ «ኢትነጽር ብእሲተ እኪተ»።

፫. ምሳ. ፮ ፥ ፬ – ፳፪

፲፯. ያዘችውም፤ ሳመችውም፤ ፊትዋም ያለ ጎፍረት ሆኖ እንዲህ አለችው ።

፲፰. የፍቅሬ መሥዋዕት ነው፤ ዛሬ ስእለቴን እሰጣለሁ።

፲፱. ስለዚህ እንድገናኝህ መጣሁ፤ ፊትህንም ስሻ አገኘሁህ።

፳. በአልጋዬ ላይ ማለፊያ ሰርፍ ዘርግቼበታለሁ፤ የግብፅንም ሽመል መሌ ምንጣፍ ዘርግቼበታለሁ።

፳፩. በመኝታዬ ዐልሙን፤ በቤቴም ቀረፋ ረጭቼበታለሁ።

፳፪.ና፤ እስኪነጋ ድረስ በመልካም መሳሳም ደስ ይበለን፤ በፍቅርም እንርካ ።

፳፫. ባለቤቴ በቤቱ የለምና፤ ወደ ሩቅ መንገድም ሄዶአልና ፤

፳፬. በእጁም የወርቅ ከረጢት ይዞ አል፤ ወደ ቤቱ ቢመለስም ከብዙ ጊዜ በኋላ ነው።

፳፭. በብዙ ጨዋታዋ ታስተዋ ለች፤ በከንፈርዋ ወጥመድም ትጎ ትተዋለች።

፳፮. እርሱም ለመታረድ እንደ ሚነዳ በሬ፤ ለመታሰርም እንደ ሚሔድ ውሻ አንገቱን ደፍቶ ይከተላታል።

፳፯. ዳግመኛም እንዲህ ይላል፣ «ወደ አመንዝራ ሴት አትመልከት»።

፳፫. እስመ መዓር ይውኅዝ እም ከናፍረ ብእሲት ዘማ፤ እንተ ለኪ ዜሁ ያመዐርዕሮ ለጉርዔከ።

፳፬. ወእምድኅሬሁሰ ዘይመርር እም ሐሞት ትረክብ፤ ወስሑል ፈድ ፋደ እመጥባሕት ዘክልኤ አፉሁ።

፳፭. ወካዕበ ይቤ ረሲ ርኁቀ ፍኖ ተከ እምኔሃ ፤ ወኢትቅረብ ኀበ ኖኅተ ቤታ።

፳፮. ከመ ኢትወስክ ለባዕድ ሕይወተክ፤ ወንብረተከ ለእለ ዘእ ንበለ ምሕረት።

፳፯. ከመ ኢይጽገቡ ነኪራን ኀይ ለክ፤ ወግማ ዚአክ ቤተ ባዕድ ኢይባእ።

፳፰. ወትኔስሕ ድኅረ አመ ደክመ ሥጋ ነፍስትክ ወትብል።

፳፱. እፎ ጸላእኩ ትምህርተ፤ ወእ ምተግሣጽ ተግኅሠ ልብየ።

፴. ወኢሰማዕኩ ቃለ ዘይሜህ ሩኒ ወይጌሥጹኒ ወኢያጽማዕኩ በእዘንየ።

፴፩. ዘእንበለ ኀሡት ኮንኩ ውስተ ኵሉ እኩይ ማእከለ ማኅበር ወእ ንግልኃ ።

፳. ምሳ. ፭ + ፲፬

፳፪. ከአመንዝራ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባልና ፤ ለጊዜው ጕረሮህን ያጣፍጠዋል።

፳፫. በኋላ ግን ከሐሞት የመረረ ሁኖ ታገኛለህ፤ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅም የተሳለ ነው።

፳፬. ዳግመኛም እንዲህ ይላል፤ መንገድህን ከእርስዋ አርቅ ፤ ወደ ቤትዋም ደጅ አትቅረብ፤

፳፭. ሕይወትህን ለሌላ እንዳት ሰጥ፤ ንብረትህንም ምሕረት ለሌ ላቸው ።

፳፮. ባዕዳን ሀብትህን እንዳይጠ ግቡ ፤ የድካምህም ፍሬ በባዕድ ሰው ቤት እንዳይገባ።

፳፯. ሰውነትህ በደከመ ጊዜ ኋላ ትጸጸታለህ፤ እንዲህም ትላለህ።

፳፰. እንዴት ትምህርትን ጠላሁ? ልቤም ከተግሣጽ እንዴት ራቀ?

፳፱. የአስተማሪዎቼንም ቃል አል ሰማሁም ፤ በጆሮቼም አላዳመጥ ሁም።

፴. በማኅበርና በጉባኤ መካከል ወደ ክፉ ሁሉ ለመድረስ ጥቂት ቀረኝ ፤

፴፯. ወይእዜኒ አብለክሙ ጎረዩ ኵሎ ሠናያተ እለ ጽሑፋት ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ከመ ኢናስትት እሎንተ ስምዓተ፤ ወኢ ንትመየጥ ውስተ ብዙኅ ነገር።

፴፰. አላ ንጽናዕ በሃይማኖት ወበ ገቢረ ሠናይ፤ ወንርኀቅ እምኵሉ ምግባር እኩይ፤ ወንኩን ንጹሓነ እምኵሉ እኩይ ወርኵስ በቅድመ እግዚአብሔር ከመ ንርከብ ሕይ ወተ ዘለዓለም።

## አንቀጽ ፫

በእንተ ከመ መፍትው አንስት ይትአዘዛ ለአምታቲሆን፤ ወይሑራ በጥበብ።

፩. ርቱዕ ብእሲት ትትአዘዝ ወት ተሐት ለምታ፤ እስመ ርእሳ ለብእ ሲት ምታ፤ ወርእሱ ለብእሲ ዘየ ሐውር በፍኖት ርቱዕ ክርስቶስ፤ ወርእሱኒ ለክርስቶስ እግዚአብ ሔር አብ።[፩] አኃዜ ኵሉ ዘሀሎ ወይሄሉ ፈጣሬ ኵሉ ምስለ ወልዱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሎቱ ዕበይ፤ ወክብር፤ ወልዕልና፤ ወስብሐት።

፪. ወአንትንሂ አንስት ተአዘዛ ለአ ምታቲክን፤ ውተቀነያ በኵሉ ወበፈ ሪሀ እግዚአብሔር ወአስተፍሥሓ አምታቲክን በሠናይ ቅኔ፤ ከመ ትርከባ ሞገሰ በጎቤሆሙ በከመ አቅደምነ ነጊረ።

፩. ፩ኛ ቆሮ. ፲፩ ÷ ፫

፴፱. አሁንም እንዲህ እላችኋለሁ፤ እነዚህን ምስክሮች እንዳናቃልል ወደ ብዙ ነገርም እንዳንመለስ በቅ ዱሳት መጻሕፍት የተጻፉትን በጎ ነገ ሮችን ሁሉ ምረጡ።

፵፰. በሃይማኖትና በጎ በመሥራ ትም እንጽና፤ ከክፉ ሥራም ሁሉ እንራቅ፤ የዘለዓለም ሕይወትንም እናገኝ ዘንድ ከክፉ ሁሉና ከር ኵሰት በእግዚአብሔር ፊት ንጹ ሓን እንሁን።

## ሦስተኛ አንቀጽ

ሴቶች ለባሎቻቸው ይታዘዙ ዘንድ፤ በቀናም ጥበብ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ እንዲገባ ይናገራል።

፩. ሴት ለባሏ በትሕትና ትታዘዝ ለሴት ራሷ ባሏ ነውና፤ በቀና መንገድ ለሚኖር ወንድም ራሱ ክርስቶስ ነው፤ ለክርስቶስም ራሱ ሁሉን ቻይ፤ የነበረና የሚኖር ገናናነትና ክብር ልዕልናና ምስጋና በሚገባው በልጁ በጌታችን በኢየ ሱስ ክርስቶስ ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር አብ ነው ።

፪. እናንተም ሴቶች ለባሎቻችሁ ታዘዙ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራ ትና በማክበር ተገዙ፤ አስቀድመንም እንደተናገርን ከእነርሱ መወደድን እንድታገኙ በበጎ አገልግሎት ባሎ ቻችሁን ደስ አሰኙ።

፫. እስመ ከመዝ ይብል ተምህጾ ሰሎ ሞን መኑ ይረክባ ለብእሲት ጽን ዕት፤ ክብርት ይእቲ እምዕንቊ ከቡር ዘብዙኅ ሜጡ ::

፬. ለእንተ ከመዝ ብእሲት ይትአ መን ባቲ ልበ ምታ ወእንተ ከመዝ እምሠናይ ምህርካ ኢታሐ ፅየ::

፭. ትረድኦ ለምታ ሠናየ በሠ ናይ፤ ወአኮ እኩየ በእኩይ በሎሉ መዋዕለ ሕይወታ::

፮ እንዘ ትቤዝት ፀምረ ወአጌ፤ ገብረት ሠናየ በእደዊሃ::

፯. ኮነት ከመ ሐመር እንተ ትት ጌበር እምርኁቅ፤ ወታስተጋብእ ላቲ ዅሎ ብዕለ::

፰. ወትትነሣእ በሌሊት ወትሁብ ሲሳየ ለሰብአ ቤታ ወግብሮን ለአ ዋልድ::

፱. ርእየት ወፍረ፤ ወተሣየጠት፤ ወእ ምፍሬ እደዊሃ ተከለት ጥሪተ::

፲. አጽኒዓ ወቀኒታ ሐቌሃ አውፅ አት እዴሃ ለግብር ::

፲፩. ጥዕመት ከመ ሠናይ ውእቱ ተቀጸ፤ መኢይጠፍእ ዘሎ ለሊተ ማኅቶታ::

፫ ተግሣጸ ሰሎሞን እንዲህ ይላ ልና፤ ልባም ሴትን ማን ያገኛ ታል? ዋጋው ብዙ ከሆነ ከከበረ ዕንቁ እጅግ የከበረች ናት ::

፬. እንደዚህ ባለችዋ ሴት የባልዋ ልብ ይታመንባታል፤ እንደዚህ ያለችውም ከመልካም ምርኮ አታጣ ንለው·ም::

፭. ዕድሜዋን ሙሉ በክፉ ላይ ክፉ ያይደለ በበጎ ላይ በጎ እየሠ ራች ባሏን ትረዳዋለች::

፮. የበግ ጠጕርንና የተልባ እግርን እያ ባዘተች በእጆችዋ መልካም ትሠራለች::

፯. እርስዋ ከሩቅ እንደምትነግድ ሀብትንም ሁሉ እንደምትሰበስብ መርከብ ሆነች::

፰. በሌሊት ትነሣለች፤ ለቤተሰብ ምጇ ምግባቸውን ትሰጣለች፤ ለሠ ራተኞችዋም ተግባራቸውን ትሰጣለች::

፱. እርሻን ተመልክታ ትገዛለች፤ ከእጆችዋም ፍሬ ጥሪትን ትተክላለች::

፲. ወገብዋንም አጽንታ ታጥቃ እጆቿን ለሥራ ታወጣለች::

፲፩. ሥራ መልካም እንደሆነ ትመ ለከታለች፤ መብራትዋም ሌሊቱን ሁሉ አይጠፋም::

፲፪. ወእደዊሃ ትሰፍሕ ዲበ ዘይበ ቀሶዕ፤ ወዕመታ ታጸንዕ ለፈቲል።

፲፫. ወእደዊሃ ትፈትሕ ለምስኪን፤ ወእራኃ ትሰፍሕ ለነዳይ።

፲፬. ወኢይቴክዝ ምታ በእንተ ቤቱ እመ፡ ኀበ ጎንደየ ወሶሎሙ እሊአሃ እሩዛን እሙንቱ በበክልኤ።

፲፭. ክዑበ ከለሜዳ ገብረቲ ለምታ ዘቢሶስ፤ ወሜላተ ገብረት ላቲ አልባሰ።

፲፮. ወዘያስተርኢ ይከውን ምታ በውስተ አናቅጽ ሶበ ይነብር ውስተ ማኅበር ምስለ ሊቃናተ ምድር።

፲፯. ሰንዱናተ ገብረት፤ ወሜ ጠት፤ወንቀብታተ ለከነናውያን፤ ወአፉሃ ከሠተት ዘበሕግ፤ ወአቀ መት ሥርዐተ ለልሳና።

፲፰. ጎይለ ወላህየ ለብሰት ወተፈ ሥሐት በመዋዕል ደኃርያት።

፲፱. ወጽፋቅ በዋኤ ቤታ ወጎበኙተ ሀሴት ኢበልዐት።

፳. ሕግ ወምጽዋት ውስተ አፉሃ፤ አፉሃ ትፈትሕ በጥበብ ወበሥ ርዐተ ሕግ።

፳፩. እጆችዋንም ወደሚጠቅም ሥራ ትዘረጋለች፤ ክንድዋንም ለመ ፍተል ታበረታለች (ታጸናለች)።

፳፪. እጆቿን ለችግረኛ ትፈታለች፤ መሐል እጅዋንም ለድሀ ትዘረጋለች።

፳፫. ባሏም በውጭ የከበረ እንደሆነ ስለ ቤቱ አይጨነቅም፤ ቤተሰቦቿ ሁሉ ዕጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸው።

፳፬. ለባልዋ ዕጥፍ ሆኖ ከተፈተለ የተልባ እግር መጐናጸፍያ ትሠራ ለች፤ ለራስዋም ከጭ ሐር ልብስን ትሠራለች።

፳፭. ባልዋ በሀገር ሽማግሌዎች መካከል በሸንጎ በሚቀመጥ ጊዜ በወደ ባባይ የታወቀ(የሚታይ) ይሆናል።

፳፮. የበፍታ ቀሚስ እየሠራች ትሸ ጣለች፤ ለከናውያንም ድግ ትሸጣ ለች፤ ሕጋዊ በሆነ ነገር አፍዋን ትከፍታለች፤ ለአንደበትዋም መጠ ንን ታደርጋለች።

፳፯. ብርታትንና ውበትን ትለብሳለች በኋላም ዘመን ላይ ደስ ይላታል።

፳፰. ወደ ቤቷ የሚገባ ብዙ ነው፤ የስንፍና እንጀራንም አትበላም።

፳፱. ሕግና ምጽዋት በአፍዋ አለ፤ አፍዋን በጥበብና ሕግ ባለው ሥርዐት ትከፍታለች።

፳፩. መምጽዋታ አልሀቀ ውሉደ ወአብ ዐለ፤ መምታ ወደሳ።

፳፪. ብዙኃት አዋልድ አጥሪያ ብዕለ፤ ውብዙኃት ገብራ ጎይለ፤ ወአንቲሰ ትፈደፍዲ፤ ወተዐደውኪ ኵሉን።

፳፫. ሕስው አሥምሮ፤ ወምኑን ላህይ፤ እስመ ብእሲት ጡዕዐ ትት ባረክ፤ ወፈራሂተ እግዚአብሔር ይእቲ ትሴባሕ።

፳፬. ሀብዋ እምፍሬ ከናፍሪሃ፤ ወይት አኰት በአናቅጽ ምታ[፩] ።

፳፭. አእምራ አእዝት ከመ ብእሲት እንተ ታፈቅር ምታ ትረክብ ክብረ በዝዘ እግዚአብሔር አምላክ።

፳፮. ዐቂ ወለብዊ ኦ ብእሲት እንተ ታፈቅሪ ወትፈቅዲ ትኩኒ መሳይምንተ ከመ ታሥምሪዮ ለእግ ዘአብሔር፤ ወኢትትመክኪ ወኢት ሠኒዪ ለኵልአ ብእሲ ፤ ወኢትልበሲ አልባስ ሠርጉ፤ ወኢትደዩ አግዕነ ውስተ እግርኪ በትዝጎርት፤ በከመ ይገብራ አንስት ዘማት ለአስሕቶ ፤ አላ ተዐቀቢ እም

፳፯. ምጽዋትዋ ልጆችን ያሳድጋል፤ ያበለጥጋልም፤ ባልዋም እንዲህ ሲል ያመሰግናታል።

፳፱. ብዙ ሴቶች ልጆች ሀብትን ሰበሰቡ፤ ብዙዎቹም ጎይልን አደረጉ፤ አንቺ ግን ትበልጫለሽ፤ ከሁሉም ትልቂያለሽ ።

፴. ውበት ሐሰት ነው፤ ደም ግባትም የተናቀ ነው፤ ብልህ ሴት ትባረካለችና ፤ እግዚአብሔርንም የምትፈራ እርስዋ ትመሰገናለች።

፴፩. ከከንፈርዋ ፍሬ ስጡአት፤ ባልዋም በዐደባባይ ይመሰገናል።

፴፪. ሴቶች ሆይ! ባልዋን የምትወድ ሴት በፈጣሪ እግዚአብሔር ዘንድ ክብርን እንደምታገኝ ዕወቁ።

፴፫. እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የታመንሽ ትሆኚ ዘንድ የምትወጂና የምትፈቅጂ ሴት ሆይ! ዕወቂ፤ አስተውዪ፤ አትመ ኪም፤ ለሌላ ወንድም አትዋቢ፤ የጌጥ ልብሶችንም አትልበሺ፤ ሴሰ ኞች ሴቶች ሰውን ለማሳት እንደ ሚያደርጉ በትዕቢት በእግርሽ ጫማ አታድርጊ ፤ ነገር ግን ሌሎች በአንቺ እንዳይሰናከሉ

---

፩. ተግሣጽ ፳፱ + ፴፩

ከሉ ምግባር እኩይ ወዝሙት፤ ከመ ኢይትዐቀፉ ብኪ ካልኣን ዳዕሙ ተዐዘዚ ለምትኪ ወአሠንዪ ሎቱ::

፳፪. ወእመሰ ትፈቅዲ አንሶስም በውስተ ማኅበር ወመራኁብት ለአ ሥግሮ ነፍስ ብዙኅ ጊዜ፤ ይመጽእ ላዕሌኪ ኵነኔ እምኀበ እግዚአብ ሔር ፤ ወትከውኒ ዘአልባ ተስፋ::

፳፫. ከመ ሶበ ረሲዕ ይወድቅ ውስተ ዐቢይ ምንዳቤ ወያመጽእ ለርእሱ ነውረ ወጽዋረ ወዝነ ኮነው እኪት ብእሲት ታመጽእ ለርእሳ ኀሣረ::

፳፬. ወከመ አንበሳ ዘይጸንሕ ወይመስጥ ከማሁ ታሠግሮሙ ለአብዳን፤ እስመ ጽሑፍ ዘይብል ከመ ቍንቍኔ ለልብስ ወከመ ነቀዝ ለዕፅ[፫] ወከማሁ ኀዘን ታማስኖ ለብ እሲ ልቦ ::

፳፭. ወዓዲ ይቤ ይኄይስ ነቢር ውስተ ገዳም እምትንበር ምስለ ብእሲት መግዐዚት ወነባቢት ወመ ዐትምት[፬]::

፳፮. ይእዜኒ ንብለክሙ አ ሕዝበ ክርስቲያን ኢትነጽሩ ፤ ወኢትትልዉ ዘማተ አንስተ::

፫. ተግሣፅ ፩ ÷ ፳
፬. ምሳ. ፳፭ ÷ ፲፱

ከክፉ ሥራ ሁሉና ከዝሙት ተጠ በቂ፤ ለባልሽም ታዘዢ፤ ለእር ሱም መልካም አድርጊለት::

፳፯. ብዙ ጊዜ ሰውን ለማሳት በጉባኤና በዐደባባይ መመላለስን ብትወጂ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ በአንቺ ላይ ቅጣት ይመጣብ ሻል፤ ተስፋ የሌላት ትሆኛለሽ::

፳፰. ዝንጉ ሰው በታላቅ መከራ እንደሚወድቅ በራሱም ነውርንና ውርደትን፤ ኀዘንንም እንደሚ ያመጣ እንደዚሁ ክፉ ሴት ለራ ስዋ ውርደትን ታመጣለች::

፳፱. ሽምቆ እንደሚነጥቅ አንበሳ እንደዚሁ አላዋቆችን ታጠምዳቸዋ ለች፤ ብል ልብስን፤ነቀዝም ዕንጨ ትን እንዲያጠፋ፤ እንዲሁም ኀዘን የሰውን ልቡና ታጠፋዋለች ተብሎ ተጽፎአልና::

፴. ዳግመኛም ከተጨቃጫቂ ከቀባ ጣሪና ከቀሙ ሴት ጋራ ከመኖር በበረሃ መኖር ይሻላል ይላልና::

፴፩. አሁንም የክርስቲያን ወገኖች ሆይ፤ ሴሰኞች ሴቶችን አትመ ልከቱ አትከተሉ እንላችኋለን::

፴፪. ወባሕቱ ርቱዕ ለእንስት ምእመናት ይትገልበባ ርእሶን በንጽሕ ወአኮ በአሠንዮ ላህየ ገጾን ወጥም ዐታት፣ ወተከህሎ ወተሠርግም ዘአልቦ ባቍዕ ውስተ መልክዕ ዘፈጠረ እግዚአብሔር፤ ወኢይግ በራ ከመዝ አላ ሰብ የሐውራ በፍ ኖት ያድንና ርእሶን እንዘ ግል ቡባት እማንቱ፤ ወዕቀባ ርእሰክን ኦ ምእመናት ወኢትትናገራ ጽልእ ወኢምስለ መኑሂ ወፈድፋደሰ ለአ ምታቲክን ::

፴፫. ኦ አንስት ኄራት፣ ወየዋሃት አምልካሁ ለእግዚአብሔር በፍ ሥሐ ወበሐሤት::

፴፬. ወእንትሙኒ ደቂቅነ ወአኃዊነ ወአዝማዲነ ወፍቁራኒነ ጎሥዋ ለክብርት ጥበብ እንተ ታሜኒ ግዕዘነ ወታበርህ አልባቢነ ፣ ወታቀርበነ ኀበ እግዚአብሔር ወታበ ውአነ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ውስተ ሕይወት ዘለዓለም ወዕረ ፍት::

## አንቀጽ ፬

በእንተ ኤጲስ ቆጶስ፣ ወቀሲስ፣ ወዲያቆናት::

፴፭. ነገር ግን ላመኑ ሴቶች ራሳቸውን በንጽሕና ሊከናነቡ ይገባል፤ የፊታቸውን ውበት በማ ሳመርና ቀለም በመቀባት አይደ ለም፤ እግዚአብሔር በፈጠረው መልክ ውስጥ ጥቅም በሌለው ኮል መኪልና ማጌጥም አይደለም ፣ እንዲህ ያለውንም ሁሉ አይሥሩ፤ ነገር ግን እነርሱ ተከናንበው በጎዳና ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ይሂዱ፤ ምእመናት ሆይ! ራሳች ሁን ጠብቁ፤ ከማንም ጋር አት ነጋገሩ ፤ ይልቁንም ከባሎቻችሁ ጋር ጥላቻን አትነጋገሩ::

፴፮. ደጋጎችና የዋሆች ሴቶች ሆይ! በደስታና በሐሴት እግዚአ ብሔርን አምልኩት::

፴፯. እናንተም ልጆቻችን፣ ወንድሞቻ ችን፤ ዘመዶቻችንና ወዳጆቻችን ጠባ ይን የምታሳምር፣ ልቡናችንን ብሩህ የምታደርግ፣ ወደ እግዚአብሔርም የምታቀርበንን ለዘለዓለም ሕይወ ትና ዕረፍት ወደ መንግሥተ ሰማ ያት የምታስገባን የከበረች ጥበ ብን ፈልጓት ::

## አራተኛ አንቀጽ

ስለ ኤጲስ ቆጶስ፣ ስለ ቄስና ስለ ዲያቆናት ይናገራል::

፩. ወበእንተ ኤጲስ ቆጶስ ሰማዕነ ከመዝ በነበ እግዚእነ ኢየሱስ ክር ስቶስ ከመ መፍትው ይኩን ኖላዌ አባግዕ ዘይሠየም ኤጲስ ቆጶስ ለዘሉ አብያተ ክርስቲያናት ዘኢልቦ ኀውር፣ ንጹሕ ወኄር፣ ወዘኢይኄሊ ትካዘ ዘዝንቱ ዓለም፤ ወዘአጠንቀቀ ፶ ዓመተ፣ወዘፈጸመ ጎደለ ውርዙት፣ ዘኢኮነ መስተዋድየ ፣ ወዘኢይነ ብብ ሐሰተ ማዕከለ አንው።

፪. እስመ ይብል ወንጌል ዘይነብብ ቃለ በከመ ረከበ ያገብኡ ሎቱ በዕ ለተ ደይን ከመ ይኩንንም[፩] ፣ ወዓዲ ይቤ እስመ እምቃልከ ትጸ ድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን፣ ወበእንተዝ ይደሉ ይኩን ዘም ሉእ ኵሉ ሠናያተ።

፫. ወእመሰ ኢየአምር መጽሐፈ ይኩን ማእምረ ወለባዌ፤ ወይኩን ዘእማዕክላይ ብእሲ ።

፬. ወእመሰ ንስቲት ሀገር ይእቲ ወኢተረክበ በውስቴታ ዘይደልዎ ጽጽስና፣ ወተረክበ እምኔሃን ማእ ምር ወጠቢብ ዘጎዳጥ ዓመታቲሁ ወስምዐ ኮኑ ሎቱ እለ የአምርዎ ከመ ይደልዎ ይሠየም ኤጲስ ቆጶስ

፭. ስለ ኤጲስ ቆጶስም፣ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የሚ ሾመው የምእመናን ጠባቂ ነውር የሌ ለበት፣ ንጹሕና ቸር፣ የዚህንም ዓለም ጭንቀት የማያስብ፣ ፶ ዓመት የሞላው፣ የጕልማሳነት ኀይልን ያለፈ፣ ነገር የማይሠራ፣ በወንድሞችም መካከል ሐሰትን የማይናገር ይሆን ዘንድ እንደሚገ ባው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ሰማን።

፮. ወንጌል ነገርን እንዳገኘ የሚና ገር ሁሉ በፍርድ ቀን ይፈረድበት ዘንድ ይመለስለታል ብሏልና፣ ዳግመኛም ከቃልህ የተነሣ ትጸ ድቃለህ፣ «ከቃልህ የተሥገም ይፈረድ ብሃል» ብሏልና፣ ስለዚህም በጎ ውን ነገር ሁሉ የተመላ ይሆን ዘንድ ይገባል።

፯. መጽሐፍ የማያውቅ ቢሆን ግን ዐዋቂና አስተዋይ ይሁን፣ መካከለኛ ዕድሜም ያለው ሰው ይሁን።

፰. አገሪቱ ትንሽ ብትሆን፣ ግን በውስጧም ጽጽስና የሚገባው ባይ ኖኝ ከታናናሾች እድሜው ጥቂት የሆነ አዋቂና ብልህ፣ የሚያውቁት ሰም ችም ኤጲስ ቆጶስነት ይሾም ዘንድ

---

፩. ማቴ. ፲፪ ÷ ፴፮-፴፯

ወለእመ ሐይወ እምንእሱ ፍጹመ በግብረ አበው ቅዱሳን ወየዋሃን ዘየሐውር በፍኖተ ርትዕ ዘምኩር በሰሉ ግብር ወስምዐ ኮኑ ላዕሌሁ ከመ ፍጹም ውእቱ ይሠየም በሰላም::

፫. እስመ ሰሎሞን እንዘ መጠነ ፲ወ፪ ዓመታቲሁ ነግሠ ላዕለ ሕዝበ እስራኤል[ደ] ፡ወኢዮአስኒ ነግሠ አመ ኮነ ሎቱ ፯ ዓመተ[ሀ] ወኢዮስያስኒ በሳምኒት ዓም ነግሠ በጽድቅ[ወ]::

፮. እስመ እግዚአብሔር ነበበ በአፈ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ ኀበ መኑ እኄድር ዘእንበለ ኀበ የዋህ ወትሑት ወጽምው ዘይርዕድ እም ቃልየ[ፀ] ::

፯. ወካዕበ ይቤ ወንጌል «ብፁዓን የዋሃነ ልብ እስመ እሙንቱ ይወርስዋ ለምድር»::

፰. ወይኩንኬ መሐሬ፡ እስመ ይቤ ብፁዓን መሐርያን፡ እስመ እሙንቱ ይትመሐሩ[ነ] ::

እንዲገለው ቢመስክሩለት ኪሳዋነ ቱም ጀምሮ በቅዱሳንና የዋሃን አበው ሥራ ፊጽሞ ቢኖር በቀና መንገድም ቢሄድ በሥራው ሁሉ የተፈተነ ቢሆን ፍጹም እንደ ሆነም ቢመስክሩለት በሰላም ይሾም::

፫. ሰሎሞንም ዕድሜው ዐሥራ ሁለት ዓመት ሳለ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ነግሦ ነበርና፡ኢዮአስም ሰባት ዓመት በሆነው ጊዜ ንጉሥ ሆነ ተሾመ ፡ ኢዮስያስም በስምንት ዓመቱ በእውነት ነገሠ::

፮. እግዚአብሔር በነቢዩ በኢሳይ ያስ አንደበት እንዲህ ብሎ ተናግ ሮአልና፡ «ከቃሌ የተነሣ ወደሚ ፈራ የዋህ፡ ትሑትና ትዕግሥ ተኛ ወደሚሆን ነው እንጂ ወደ ማን እመለከታለሁ?

፯. ዳግመኛም ወንጌል እንዲህ ይላል «የዋሆች ብፁዓን ናቸው፡ እነርሱ ምድርን ይወርሳሉና»::

፰. የሚምር ይሁን፡ «የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፡ እነርሱም ይማ ራሉ» ተብሏልና::

---

ደ. ፪ኛ ነገሥ. ፫ + ፳
ሀ. ፪ኛ ዜና መዋ. ፴፬ + ፩
ወ. ፪ኛ ነገሥ. ፳፪ + ፩ — ፪
ፀ. ኢሳ. ፶፯ + ፪
ነ. ማቴ. ፭ + ፯

፱. ወይኩን እንከ ገባሬ ሰላም፤ እስመ ይቤ ብፁዓን ገባርያነ ሰላም፤ እስመ እሙንቱ ውሉደ እግዚአብሔር ይሰመዩ»[፭] ::

፲. ወይኩን እንከ ንጹሐ ልብ ዘእንበለ ቂም ወእከይ ወዐመፃ፡« እስመ ይቤ ብፁዓን ንጹሓነ ልብ፤ እስመ እሙንቱ ይሬእይዎ ለእግዚአብሔር» ፤

፲፩. ወይኩን እንከ መንፈሳዊ ትጉህ ለገቢረ ሠናይ ዘኢሰሉዕ ወኢመዓትመ፤ ወኢሰካሬ፤ ወኢ መስተበቅለ ዘአልቦ ጽልእ ወጋዕዝ ወኢዝኅር፤ ወኢመፍቀሬ ወርቅ፤ ወኢጸዓሌ፤ ወኢይትዐበይ እንከ ከመ ኢይደቅ ውስተ መሥገርተ ሰይጣን እስመ ዙሉ ዘአዕበየ ርእሶ የኀሥር ወዘአትሐተ ርእሶ ይከ ብርኂ ::

፲፪. ወከመዝ ይሠየም ኤጲስ ቆጶስ ዘአሐተ ብእሲተ አውሰበ፤ ዘይክል ሠሪዐ ቤቱ በሠናይ፤መምህር ወመገሥፅ ዘአልሐቀ ደቂቆ በንጽሕ[፬]::

፲፫.ሰላምን የሚያደርግ ይሁን "ሰላ ምን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይባ ላሉ " ተብሏልና::

፲. ቂም፤ ክፋትና ዐመፅ የሌለበት ልበ ንጹሕ ይሁን፤ ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው እነርሱ እግዚአብ ሔርን ያዩታል ተብሏልና ::

፲፩.በጎ ሥራን ለመሥራት ትጉህ መንፈሳዊ ይሁን የማይሳሳ፤ የማ ይቆጣ ፤ የማይሰክር ፤ የማ ይበቀል፤ ጸብና ክርክር የሌለው፤ የማይኮራ፤ ገንዘብ የማይወድ፤ የማይሳደብ ይሁን፤ በሰይጣን ወጥመድ እንዳይወደቅ ፤ አይ ታበይ፤ ራሱን ከፍ ያደረገ ይዋ ረዳልና፤ ራሱንም ያዋረደ ይከብ ራልና ::

፲፪. እንደዚህ ያለ ኤጲስ ቆጶስ አንዲት ሴት ያገባ ቤተሰቦቹን በመልካም ማስተዳደር የሚችል ፤ የሚያስተምርና የሚመክር ልጆቹን በንጽሕና ያሳደገ ይሾም::

---

፭. ማቴ- ፭ ÷ ፱

፮. ፩ኛ ጢሞ. ፫÷፪–፯ ፤ ሉቃ. ፲፮÷፲፱

፬. ቲቶ ፩ ÷ ፮

፲፫. ወበእሲቱኒ ትኩን መሐይም ንተ እንተ ተሐፅን ደቂቃ በሠናይ አምልኮ ወፈሪሀ እግዚአብሔር፣ ወርቱዕ ለኤጲስ ቆጶስ ይትአዘዙ ሎቱ ሰብእ ቤቱ በትሕትና ወበ ፍርሀት፣ ወውእቱኒ ይኩን ዘአ ልቦ ነውር በትካዘ ዝ ዓለም ወበ ሥጋሁ፣እስመ ጽሑፍ ይፍትኖ ወያመክሮ እመ ውእቱ ዘአልቦ ነውር ወኢይኩን መዓትመ ከመ ይብል ጥበብ እስመ መዓትም ብእሲ ጠቢበ የሀጕል[1] አላ ይኩን መሐሬ ወመጽዋቴ፣ እስመ ይቤ እግዚእነ በዝንቱ የአምረክሙ ዘሉ ከመ አርዳእየ አንትሙ ለእመ ተፋቀርክሙ በበይናቲክሙ[፲፩]::

፲፬. ይኩንኬ መፍቀሬ ሰብእ፣ ዘይት ዌከፍ ነግደ፣ ዘኢይነሥእ ገጸ መበይነ፣ ዘኢያደሉ ለባዕል ወለነ ዳይ፣ ዘቦ ኪን ዘይሰፍሕ እደሁ ለውኂብ ፣ ዘይትዌከፍ መዓስበ መፍቀሬ ነዳያን ወዕገለ ማውታ፣ ወመበለታት፣ ወዓዲ ይሴሲ ለእለ ቦን ደቂቅ ::

[1] ምሳ. ፲፰ + ፲፯

[፲፩] ዮሐ. ፲፫ + ፴፭

፲፭. ሚስቱም የምታምን፣ ልጆቿንም በመልካም አምልኮና እግዚአብሔ ርን በመፍራት የምታሳድግ ትሁን፤ ለኤጲስ ቆጶሱም ቤተሰቦቹ በትሕ ትናና በፍርሃት ይታዘዙለት ዘንድ ይገባል፤ እርሱም በዚህ ዓለም ጉዳይና በሥጋው ነውር የሌለበት ይሁን፤ ነውር የሌለበት እንደሆነ ፈጽመህ መርምረው ተብሎ ተጽ ፎአልና ፤ የማይቄጣ ይሁን፤ መጽሐፈ ጥበብ «ቊጣ ጥበበኛ ሰውን ያጠፋል» ብሏልና፤ ነገር ግን የሚራራና የሚመጸውት ይሁን፤ ጌታችን «እናንተ እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ ደቀ መዛ ሙርቴ እንደሆናችሁ ሁሉ በዚህ ያውቃችኋል» ብሏልና::

፲፮. ሰውን ወዳጅ፣ እንግዳን የሚቀ በል፤ ፊት አይቶ የማያዳላ፣ ሰባለጸጋና ደሃ የማያዳላ፣ ፈራጅ፣ ጥክዘ ያለው፤ ለመሥጠት እጁን የሚዘረጋ፣ ረዳት የሌለውን የሚቀበል፣ ድሆችን፣ ደሀ አደጎችንና ባልቴቶችን የሚወድ ይሁን፤ ዳግመኛም ልጆች ያሏቸ ውን ይመግብ፤

፲፮. ወእመሰ ቦ ብእሲ ሀካይ ወአኀለቀ ኵሉ ንዋዮ በስካር ወዝሙት፤ ወይፈቅድ ይመጽው ትዎ ፤ ኢየሀቦ ኤጲስ ቆጶስ ትካዞ፤ወኢያብሉ ይባእ ቤተ ክር ስቲያን፤ እስመ ይብል መጽሐፍ ለእለ ይገብሩ ከመዝ እስከ ማእ ዜኑ ሀካይ ትሰክብ ወማእዜ እምንዋም ትነቅሕ? ሕቀ ትነ ውም፤ወሕቀ ትነብር ሕቀ ትዴቅስ፤ ወሕቀ ታስተጋብእ እዴከ ዲበ እን ግድዓከ፤ ወእምዝ ይመጽእከ ከመ እኩይ ሐዋርያ ንዴት ወተጽናስ ከመ ኄር ረዋሚ[፲፪]።

፲፯.ኢርቱዕ ለኤጲስ ቆጶስ ከመይፍ ታሕ በእድልዎ ለገጸ ባዕል፤ ወይ ትንየይ ነዳየ፤እስመ ይቤሎ እግ ዚአብሔር ለሙሴ ኢትፍታሕ በእድ ልዎ ለገጸ ባዕል ወኢትግምጽ ፍትሖ ለነዳይ እስመ ፍትሕ ለእግዚአብሔር ውእቱ፤ ወባሕቱ መፍትው ይፍታሕ በርትዕ።

፲፰. መፍትው ይኩን ሲሳዩ ለኤ ጲስ ቆጶስ መብልዕ ጥዑመ በእቅም ከመ ይክሃል ምህሮ ወገሥጾ ለሕዝብ ወይሚጦሙ ለኀበ እግዚአብሔር ወይርኀቅ እምኵሉ እኩይ ወያንብብ መጻ ሕፍተ ኵሉ ጊዜ።

፲፱.ገንዘቡን ሁሉ በስካርና በዝሙት የጨረሰ ሰነፍ ቢኖር ግን፤ ሲመጻ ውቱትም ቢወድ፤ኤጲስ ቆጶሱ ግዳጁን አይስጠው፤ወደ ቤተ ክር ስቲያንም ይገባ ዘንድ አይፍቀድ ለት፤ እንደዚህ ለሚሠሩ መጽ ሐፍ እንዲህ ይላልና ፤ «ሰነፍ እስከመቼ ድረስ ትተኛለህ? መቼስ ከእንቅልፍህ ትነቃለህ? አንድ ጊዜ ትተኛለህ ፤ አንድ ጊዜ ትቀመ ጣለህ፤ አንድ ጊዜ ታንቀላፋለህ፤ አንድ ጊዜ እጅህን በደረትህ ላይ ትሰበስባለህ፤ ከዚህ በኋላ ድህነት እንደክፉ መልእክተኛ ይመጣብ ሀል፤ ችጋርም እንደፈጣን ሯጭ ይደርስብሀል»።

፳. ኤጲስ ቆጶሱ ደኃውን ችላ ብሎ ሰባለጸጋው ፊት በማድላት ይፈርድ ዘንድ አይገባውም፤ እግዚአብሔር ሙሴን «ለባለጸጋ ፊት በማድላት አትፍረድ፤ የድኃውን ፍርድም አታ ጓድል፤ ፍርድ የእግዚአብሔር ነው ብሏልና ፤ ነገር ግን በሚገባ ይፈርድ ዘንድ ይገባዋል።

፳፩. የኤጲስ ቆጶስ ምግቡ የጣመ የላመ ይሁን፤ መጥኖ ይመገብ፤ ሕዝቡን መክሮ አስተምሮ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ይቻ ለው ዘንድ፤ ከክፉም ሁሉ ይርቅ ዘንድ መጻሕፍትን ሁል ጊዜ ይመልከት ።

---

፲፪. ምሳሌ ፮ ÷ ፱–፲፩

፲፰. ወይኩን መፍቀሬ ጥበብ ከመ ይክሃል ተርጕሞ መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ ፣ ቃለ ወንጌል አሪተ ወነቢያተ በከመ ይቤ እግዚ አብሔር ለብዉ ቃለ መጻሕፍት እስመ እሙንቱ ስምዕ በእንቲ አየ[፲፫] ::

፲፱. ወይደልዎ ለኤጲስ ቆጶስ የሐሊ ተጋሥሦ ወአገንጽሎ መጻሕፍት በበመትልው፤ ወያጽግቦሙ ለሕዝብ ትምህርተ መንፈሳዊ ወያርውዮሙ እምብርሃነ ሕጉ ለእግዚአብሔር በብ ዙኅ ተግሣጽ::

፳. ይቤ እግዚአብሔር አብርሁ ብርሃነ ጥበብ ላዕሌክሙ እስመ ጊዜሁ ውእቱ[፲፬] ::

፳፩. ከመዝኬ ርቱዕ ለኤጲስ ቆጶስ ይሕምም ወይጸሙ ወይትጋደል በእንተ ጽድቅ፤ወፈድፋደሰ በቅድመ ሕዝብ፡ ከመ ይርአዩ ግብሮ ወይት ወከፉ ተግሣጸ ::

፳፪. ወኀዲ ውእቱሰ ኢይትሀከይ መካሂ፤ ወኢይትዐረክ ምስለ ዐቢያን፤ወኢይኩን ዘከልኤ ልቡ ወዘከልኤ ልሳኑ

፲፯. በመንፈስ ቅዱስ መጻሕፍትን መተርጐም ይችል ዘንድ ጥበብ መንፈሳዊን የሚወድ ይሁን ፤ የወንጌልን ቃል አሪትን ነቢያትንም መተርጐም ይችል ዘንድ እግዚአብሔር እንዳለ የመጻሕፍትን ቃል አስተውሉ እነሱ ስለ እኔ ነገር ምስክሮች ናቸውና::

፲፱. ለኤጲስ ቆጶስ መመራመርና መጻሕፍትንም ዘወትር መመልከትን ያስብ ዘንድ ይገባዋል፣ ለሕዝቡም መንፈሳዊ ትምህርትን ያጥግባቸው፤ ከእግዚአብሔር ሕግ ብርሃንነት የተነሣም በብዙ ምክር ያርካቸው ::

፳.እግዚአብሔር ጊዜው ነውና የጥበብን ብርሃን በእናንተ ላይ አብሩ አለ ::

፳፩. ለኤጲስ ቆጶስ እንደዚህ መከራ ሊቀበል፤ ሊደክምና ስለጽድቅም ሊጋደል ይገባዋል፤ ይልቁንም በሕዝቡ ፊት፣ ምክሩን ይቀበሉ ዘንድ ሥራውን ሊያሳያቸው ይገባል::

፳፪. እሱ ማንንም ቸል አይበል፤ ከታላላቆች ጋርም አይወዳጅ፤ ሁለት ልብና ሁለት አንደበት ያለው

---

፲፫. ዮሐ. ፭ ÷ ፴፱
፲፬. ሆሴዕ ፲ ÷ ፲፪

ወኢይትሉ መኳንንተ ፤ ወይፍራህ እግዚአብሔር፤ ወኢይስማዕ ውዴተ በሐሰት ላዕለ ካልእ ወኢይትህከይ ጸዊመ፤ ወኢያመክኒ ለበሊዕ፤ ወኢይበል በዓል ዮም በከመ ይገብሩ አሕዛብ ለበሊዕ ወሰትይ ወለፈጊዕ ::

፳፫. አላ ያሰስል እምኔሁ ዙሉ ፍትወተ ጽሩዐ ዘአልቦ ባዕዕ፤ እስመ ዝንቱ ዙሉ ምኑን ወጽሉእ በጎበ እግዚአብሔር ወፍቁር በጎበ አጋንንት::

፳፬. ይደልዎ ለኤጲስ ቆጶስ የአዝዞሙ ወይገሥጾሙ ለሕዝብ ያዕትት እምላዕሌሆሙ ዘንተ ዙሉ ምግባረ አላ ባሕቱ ይምህሮሙ ወይገሥጾሙ፤ ወይሚጦሙ ይትመሰሉ ኪያሁ፤ ወይትልዉ ፍኖቶ በርትዕ፤ እስመ ይቤሎሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል "ዕቀቡ ሕግየ ወሥርዐትየ ወትእዛዘየ[፲፯]፤ ወለሊሁ እግዚእነ ወአምላክነ ኢየሱስ ክርስቶስ አቅደመ ዙሉ ገቢረ ወመሀረነ ንትመሰል ኪያሁ ::

፳፭. ወበእንተዝ ይብል እስመ ዘይሜህር ወይገብር ዐቢየ ይስውን በመንግሥተ ሰማያት[፲፰]::

፲፯. ዘዳግ. ፮÷፲፯

፲፰. ማቴ. ፭÷፲፱

አይሁን፤ መኳንንቱንም አይከተል፤ እግዚአብሔርን ይፍራ፤ በለሎሙም ላይ በሐሰት ነገር ሥራን አይስማ፤ ጸምንም ቸል አይበል፤ ለመብላትም ምክንያት አያድርግ፤ አሕዛብ ለመብላት ለመጠጣት፤ ተድላ ደስታ ለማድረግ በአልን ምክንያት እንዲያደርጉ «ዛሬ በዓል ነው እንብላ» አይበል::

፳፬. ነገር ግን ጥቅም የሌለው የስንፍና ምኞትን ከእርሱ ያርቅ፤ ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ በአጋንንት ዘንድ የተወደደ ነውና ::

፳፭. ለኤጲስ ቆጶስ ይህንን ሁሉ ሥራ ከእነርሱ ያርቅ ዘንድ ሊያዝዟቸውና ሊመክራቸው ይገባዋል፤ ነገር ግን እሱን ይመስሉ ዘንድ፤ አካሄዱንም በቅንነት ይከተሉ ዘንድ ይገስጻቸውና ያስተምራቸው እንጂ፤ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ሕጌን ሥርዓቴንና ትእዛዜን ጠብቁ ብሎአቸዋልና፤ እሱ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም በጎ ሥራን ሁሉ አስቀደመ፤ እርሱንም እንመስል ዘንድ አስተማረን ::

፳፮. ስለዚህም የሚያስተምረውን የሚሠራ ሰው በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይሆናልና ይላል ::

፳፮. ርቱዕ ለክሙ ለኤጲስ ቆጶሳት ትምህርምሙ ለሕዝብ ወታድጎ ንምሙ እምስሕተት በከመ ጸገወ ክሙ ለክሙ ክርስቶስ ::

፳፯. እስመ እግዚአብሔር ነበበ በአፈ ሕዝቅኤል ነቢይ ወይቤ ወልደ እጓለ እመሕያው ሰብአ ዐይን ረሰይኩከ ለቤተ እስራኤል ከመ ትስማዕ ቃለ እምአፉየ ወት ገሥጾሙ በቃልየ ::

፳፰. ወእምከመ እቤሎ ለኃጥእ ሞተ ትመውት ወእመ ኢነገርኮ ለኃጥእ ወኢገሠጽኮ ከመ ይነስሕ ወይትመየጥ እምፍኖቱ እኩይ ወይሕየው ፣ ውእቱኒ ኃጥእ ይመውት በኀጢአቱ ወደሞ እት ኀሠሥ እምኔከ ይቤ እግዚአ ብሔር::

፳፱. ወእመሰ ገሠጽኮ ለኃጥእ ወኢተመይጠ እምኀጢአቱ ይመ ውት በጌጋዩ፤ ወአንተሰ ታድኅን ነፍስከ ::

፴. ወእመ ተመይጠ ጻድቅ እም ጽድቁ ወገብረ ኀጢአተ እንዘ አር እዮ መቅሠፍትየ ቅድመ ገጹ ወኢገሠጽኮ ሞተ ይመውት

፴፩. ኤጲስ ቆጶሳት ሕዝቡን አስተ ምራችሁ ከስሕተት ታድኖአቸው ዘንድ ለእናንተ ይገባል፤ ክርስቶስ ለእናንተ እንደሰጣችሁ መጠን::

፴፪. እግዚአብሔር በነቢዩ በሕዝ ቅኤል ቃል የሰው ልጅ ሆይ! ቃሌን ከእኔ አፍ ሰምተህ በቃሌ ትገሥጻቸውና ትመክራቸው ዘንድ ለእስራኤል ወገኖች ጉበኛ አደረ ግሁህ » ብሎ ተናግሮአልና ::

፴፫. እግዚአብሔርም አለ፣ ኃጥኡን ሞትን ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ፣ ንስሓ እንዲገባና ከክፉ መንገዱ እንዲመለስ ባትነግረውና ባትገ ሠጸውም ያም ኃጥእ በኃጢአቱ ሳለ ቢሞት ደሙን ከአንተ እፈል ጋለሁ ይላል እግዚአብሔር::

፴፬. ኃጥኡን ግን መክረኽውና ገሥፀኽው ሳይመለስ በበደሉ እን ዳለ ቢሞት አንተ ነፍስህን አዳ ንክ::

፴. ጻድቁም ከጻድቅነቱ ወጥቶ ኀጢ አትን በሠራ በፊቱ መቅሠፍቴን እያ ሳየሁት በበደሉ እንዳለ ይሞት ዘንድ ባትመክረው ፣ ባትገሥፀውም

በጌጋዩ ፤ ወኢይዜከር ጽድቆ ዘገብረ ውእቱ ወእትነሥሥ ደሞ እምእዴከ፤

፴፪. ወእመኒ ገሠጽኮ ለጻድቅ ከመ ኢየአብስ ወኢአበሰ ውእቱኒ ጻድቅ ሕይወተ የሐዩ፤ ወአንተኒ አድኀንከ ነፍሰከ[፲፯] ::

፴፫. ኮነዙኪ ሰብ ይሐውን ቀትል ወጸብአ ማዕከለ ሕዝብ እሙንቱ የኀሥሡ ሰብአ ዐይን ዘይዜን ምሙ ከመ ይትዐቀቡ፤ ወእመሰ ኢቀደመ ነጊሮቶሙ ከመ ይድኀኑ እምቀትል ደሙ እምላዕለ ርእሱ፤ እስመ ኢሰምዑ ቃለ ቀርን ::

፴፫. ወባሕቱ ዘሰ ርእየ ኵናተ እንተ ትመጽእ ላዕለ ብሔር ወይነፍሕ በቀርን ትእምርተ ለሠራዊት ወሰምዐ ዘይሰምዕ ቃለ ቀርን ወኢተግኅሠ ወመጽአ ኵናት ወረከበቶ ይገብእ ደሙ ላእለ ርእሱ፤ እስመ ሰምዐ ቃለ ቀርን ወኢተግኅሠ ወደሙ ይሰወጥ ዲቤሁ፤ ወዘንቱሰ እስመ ተግሕሠ አድኀነ ነፍሶ[፲፰] ::

፲፯. ሕዝ. ፴፫ ፡ ፮ - ፱ ፤ ፫ ፡ ፲፯–፲፱

፲፰. ሕዝ. ፴፫ ፯

እርሱም ያደረገውን ጽድቁን አላስብለትም ደሙን ከአንተ እጅ እፈልጋለሁ::

፴፬. ጻድቁን ግን እንዳይበድል ብትገሥጸው ብትመክረው እርሱ ከሞት ይድናል፤ አንተም ነፍስህን አዳንህ ::

፴፭. እንደዚሁም በሕዝቡ መካከል ጦርነትና ውጊያ በተደረገ ጊዜ እነርሱ ይጠበቁ ዘንድ የሚነግራቸው ጉበኛን ይፈልጋሉ፤ ከሞት ይድኑ ዘንድ፤ ባይነግራቸው ግን ደሙ በራሱ ላይ ነው የመለከት ድምጽን አልሰሙምና::

፴፮. ነገር ግን በሀገር ላይ የምት መጣ ጦርን ያየ ለሠራዊቱ ምልክት መለከትን ቢነፋ፤ የመለከቱን ድምፅ ሰምቶ ገለል ባይል፤ ጦርም መጥታ ብታገኘው፤ ደሙ በራሱ ላይ ነው ፤ የመለከቱን ድምፅ ሰምቶ ገለል አላለምና ደሙ በላዩ ላይ ይመለሳል፤ እርሱ ግን ገለል ብሏልና ነፍሱን አዳነ::

፴፬. ከማሁ ውእቱ ኤጲስ ቆጶስ ለእመ መሀረ ቃለ ሕይወት ይረ ክብ ሕይወተ ዘለዓለም፤ ወኵናትሰ ኵነኔ ውእቱ ዘለዓለም ፤ ወቃለ ቀርንኒ ወንጌል ቅዱስ፤ ወሰብአ ዐይንኒ ኤጲስ ቆጶስ ውእቱ ለቅ ድስት ቤተ ክርስቲያን፤ መፍትው ለኤጲስ ቆጶስ ይርዐይ ወይምሀር ወያጽንዕ ቃለ መጻሕፍት ወያፍ ርህ በእንተ ኵነኔ፤ ወበእንተዝ ይገሥጾሙ ለእለ የሐውሩ ዘእንበለ አእምሮ፤ ወያርእዮሙ ክሡተ፤ ወለ እለ ኢየአምሩ ይምህሮሙ ፤ ወለ እለ የአምሩ ያጽንዖሙ፤ ወለእለ ተገድፉ ያስተጋብኦሙ፤ ወይንግ ሮሙ ኵሎ ጊዜ በእንተ መድ ኀኒቶሙ ከመ ሶበ ሰምዑ ዘንተ ተግሣጸ ይግበሩ ሠናየ።

፴፭. እስመ ይቤ እግዚአብሔር በነቢይ አስምዕ ላዕለ ዝንቱ ሕዝብ ወንግሮሙ ኀጢአቶሙ ለእመ ይትመየጡ ወይኔስሑ ወይድኅኑ እምጌጋዮሙ[፲፱]።

፴፮. ወዓዲ ይቤሎሙ ሙሴ ለሕ ዝብ ስማዕ እስራኤል እግዚአ ብሔር አምላክከ ፩ ውእቱ[፳]።

፴፯. እንደዚሁም ኤጲስ ቆጶሱ የሕይወትን ቃል ወንጌልን ቢያስተ ምር የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛል፤ ጦሩም የዘለዓለም ፍዳ ነው፤ የመ ለከቱም ድምፅ ቅዱስ ወንጌል ነው ፤ ጉበኛ ሰላዩም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ነው፤ ኤጲስ ቆጶሱ ስለ ፍርድም እያስ ፈራ ቃሉንም እያጠና ያስተምርና ይጠብቅ ዘንድ ይገባዋል ፤ ስለዚህም ነገር ባለማወቅ የሚኖሩትን ሰዎች ይምከራቸው፤ ገልጾም ያስረዳቸው፤ የማያውቁትን ያስተምራቸው፤ የሚ ያውቁትንም ያጽናቸው፤ የተበተኑት ንም ይሰብስባቸው፤ ሁልጊዜም ስለድኅነታቸው ይንከራቸው ፤ ይህን ተግሣጽ በሰሙ ጊዜ በጎ ሥራን ይሠሩ ዘንድ ።

፴፰. እግዚአብሔር በነቢዩ አድሮ በዚህ ሕዝብ ላይ አዳኝበታለሁ፤ ምን አልባት ከኀጢአታቸው ቢመለሱ ንስሐ ገብተውም ቢድኑ ኃጢአታ ቸውን ንገራቸው ብሏልና።

፴፱. ዳግመኛም ሙሴ ሕዝቡን እስራኤል ሆይ ስማ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አንድ ነው አላቸው አንድ እግዚአብሔር ነው።

---

፲፱. ኢር. ፴፩ ÷ ፫

፳. ዘዳግ. ፮ ÷ ፬

፴፯. ወካዕበ ይቤ በወንጌል ቅዱስ ዘቦ እዝን ሰሚዐ ለይሰማዕ[፳፩]::

፴፰. ወሰሎሞን ይቤ ስማዕ ወል ድየ ተግሣጸ አቡከ፤ ወኢትትሀየይ ትእዛዘ እምከ፤[፳፪] ወኢሰምዑ እስከ ዛቲ ዕለት፤ ወጎደግዎ ለእግ ዚአብሔር ለፅ ዘበአማን አምላክ ርቱዕ ::

፴፱. ወሰመዮሙ ትውልደ ዐላው ያን ወዘማውያን ዘአቅደምነ ነጊረ በእንቲአሆሙ፤ ወይእዜኒ አእምሩ አ ፍቁራኒነ እለ ተጠመቅሙ በሞቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስ ቶስ እስመ ኢርቱዕ የአብሱ እለ ነሥኡ ዘከመዝ ጸጋ::

፵. አእምሩ አኀዊነ እስመ እምድ ኅረ ነሥኡ ጥምቀተ ሕይወት ወገ ብኡ ውስተ ግብረ ኀጢአት ይወ ርዱ ውስተ ኵነኔ ገሀነም ::

፵፩. ወባዕዳንሂ እለ ኢኮኑ መሃይ ምናነ ወእምዝ አምኑ ወተጠምቁ ይከውኑ ብፁዓነ በቅድመ እግዚአ ብሔር፤ በስመ ይቤ እግዚእነ በወ ንጌል ቅዱስ «ብፁዓን አንትሙ ሶብ ይጸእሉክሙ፤ወይዘነጕጉክሙ፤ወ ይነቡ ኵሉ እኩየ ላዕሌክሙ እንዘ ይሐስዉ በእንቲአየ ተፈሥሑ እስመ ብዙኅ ውእቱ ዕሤትክሙ በሰማያት»[፳፫] ::

፵፪. ዳግመኛም በቅዱስ ወንጌል ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ አለ።

፵፫. ሰሎሞንም ልጄ፤ የአባትህን ተግሣጽ ስማ፤ የእናትህንም ትእ ዛዝ ቸል አትበል አለ፤ እነርሱ ግን በውነት የባሕርይ አምላክ የሚሆን አንድ እግዚአብሔርን ካዱት እንጂ እስከዚች ቀን ድረስ በሚገባ አልሰ ሙም::

፵፬. አስቀድመን ስለእነርሱ የተና ገርንላቸው የሴሰኞች የወንጀለኞች ልጆች አላቸው፤ አሁንም በጌታ ችን በኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ በምትመሰል ጥምቀት የተጠመቃ ችሁ ወዳጆቻችን ሆይ፤ አስተውሉ፤ እንደዚህ ያለ ልጅነትን የተቀበሉ ሰዎች ይበድሉ ዘንድ አይገባምና::

፵. ወንድሞቻችን ሆይ ዕወቁ፤ ካመኑ ከተጠመቁ በኋላ ወደ ኃጢአት ሥራ ቢመለሱ ወደ ገሀ ነም ፍርድ ይወርዳሉና::

፵፩. ምእመናን ያልሆኑ ሌሎ ችም ከዚህ በኋላ ቢያምኑና ቢጠ መቁ በእግዚአብሔር ፊት ጻውዳን፤ ክቡራን ይሆናሉ፤ ጌታችን በወን ጌል ንዑዳን ክቡራን ናችሁ እን ዳለ፤ በእኔ ምክንያት ቢሰድቧ ችሁ ቢያሸሟጥጧችሁ የኔን ነገር ሀሰት ነው አያሉ በናንተ ላይ በተናገሩ ጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ዋጋ ችሁ በመንግሥተ ሰማያት ብዙ ነውና»::

---

፳፩. ማቴ. ፲፩–፲፭
፳፪. ምሳ. ፩ + ፫
፳፫. ማቴ ፭ + ፲፩–፲፪

፴፪. ወእመሰ ቦ ዘነበበ ሐሰተ ላዕሌሁ ብፁዕ ውእቱ፤ እስመ ጽሑፍ ዘይብል ኮሉ ብእሲ ዘኢኮነ ምኩረ ኢኮነ ጎሩየ በጎበ እግዚአብሔር [፴፬] ::

፴፫. ወለእመ ቦ ዘወፅአ እምሕግ ወረገምዎ ለሊሁ ለርእሱ አምጽአ መርገመ፤ ከማሁ ንሕነኒ ለእመ ኢሰማዕነ ትእዛዛቲሁ ለእግዚአብ ሔር ወኢገበርነ ፈቃዶ ናመጽእ ላዕሌነ መርገመ ::

፴፬. ወዓዲ ንከውን ርጉቃነ እም እግዚአብሔር፤ እስመ ዘለሊሆሙ ይሜህሩ ኢይገብሩ[፴፭] ፤ ወኢይት መየጡ እምግዕዞሙ ::

፴፭. ኢመፍትው ለኤጲስ ቆጶስ ይገሥጾሙ ወያስተጎፍሮሙ ለእለ ይገብሩ ከመዝ፤ አላ ርቱዕ ይሙ ሆሙ በፍቅረ ክርስቶስ በከመ ይደሉ ለተቀንዮ::

፴፮. ርቱዕ ለኤጲስ ቆጶስ ይጎ ሥሥ ጽድቀ፤ ወኢያክብሮሙ ለዕ ልዋን፤ ወኢያድሉ በውስተ ፍትሕ ወኢይጕሃእ ሕልያነ በጎበ

፴፯. ሰው አሰትን በላዩ የተናገ ረበት ቢኖርም ብፁዕ ነው፤ «በመከራ ያልተፈተነ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠ አይደለም» የሚል ጽሑፍ አለና::

፴፰. ከሕግ ወጥቶም የረገሙት ሰው ቢኖር እርሱ ለራሱ ርግ ማንን አመጣ፤ እኛም እንደርሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ሰም ተን ፈቃዱን ባንፈጽም በላያችን ርግማንን እናመጣለን::

፴፱. ዳግመኛም ከእግዚአብሔር የተ ለየን እንሆናለን፤ እነርሱ የሚያ ስተምሩትን የማይሠሩ፤ ከልማ ዳቸውም የማይመለሱ ናቸውና::

፵. ለኤጲስ ቆጶሱ እንደዚህ የሚ ሠሩትን ይቈጣቸውና ያሳፍራ ቸው ዘንድ አይገባውም፤ነገር ግን ለአምልኮት እንደሚገባ በክርስቶስ ፍቅር ያስተምራቸው እንጂ ::

፵፩. ለኤጲስ ቆጶሱ እውነትን ይመረምር ዘንድ ይገባዋል፤ ከሃድ ያንንም አያክብራቸው፤ በፍርድ ጊዜም አያድላ፤ ከማንም መማለ

---

፴፬. ያዕ. ፩+፲፫ ፤ ዕብ. ፲፪+፳
፴፭. ማቴ. ፳፫–፫

መኑሂ፤ እስመ ሕልያን የዐውር አዕይንቲሆሙ፤ ለጠቢባን፤ ወያ ጸንን ነገረ ፍትሕ ወርትዕ፤ ወዓዲ ቦ ኀበ ይብል አዕትቱ እምኔክሙ ኵሉ እኩየ[፳፩]::

፴፮. ወሰሎሞንሂ ይቤ ኀበ መካን እንተ ግዕዙ ኢትሑር ህየ፤ ተገ ኀሥ እምኔሆሙ ውተመየጥ እስመ ኢይነውሙ እመ ኢገብሩ እኩየ ወይርኅቅ ንዋም እምአዕይንቲ ሆሙ፤ ወኢይነውሙ ይበልዑ መብልዐ ኀጢአት ::

፴፯. ወእመሰ ኢለበወ ኤጲስ ቆጶስ ወሖረ በትምይንት፤ወመ ናኔ ኮነ በስመ ገብረ ሳኦል ለአጋግ[፳፪]፤ ወኤሊ ካህን ዘኢገ ሠጸሙ ለደቂቁ እለ ኀደጉ ትእዛዘ እግዚአብሔር[፳፫]፤ ወናሁ ከመውሕቱ ለኢሁ ሀሁለ ክብር፤ ወዓዲ ደብተራሁ፤ ቅድስተ ዝሀገሩ ወብረ ዓመፃ በቅድመ፤

፳፩. ዘዳ. ፳፫ ÷ ፮ – ፰

፳፪. ፩ኛ ሳሙ. ፲፭–፴፬

፳፫. ፩ኛ ሳሙ. ፪÷፳፬–፳፭፤ ፬÷፲–፲፩

ጻን አይቀበል፤ መማለጃ መቀበል የአዋቂዎችን ዓይኖች ያሳውራ ልና፤ የቀናውን የፍርድ ነገርም ያጣ ምማልና፤ ዳግመኛም ክፋትን ሁሉ ከእናንተ አርቁ የሚል አንቀጽ አለና ::

፴፮. ሰሎሞንም እንዲህ አለ «እነ ርሱ በተጓዙበት ቦታ ወደዚያ አት ሂድ፤ ከእነርሱም ፈቀቅ በል ተመ ለስም፤ክፉ ካላደረጉ አይተኙምና ከዓይኖቻቸውም እንቅልፍ ይወገ ዳል፤ አይተኙምም የኃጢአትን መብል ይመገባሉ ::

፴፯. ኤጲስ ቆጶሱ ባያስተውል በተንኰልም ቢሔድ ፤ ሳኦልም በአ ጋግ እንደ አደረገ፤ ካህኑ ኤሊም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተዉ ልጆቹን እንዳልገሠጻቸው፤ እንደ ካህኑ ኤሊ ናቂ ቢሆን እነሆ እርሱ ክብሩን ያጣል፤ ዳግመኛም የሀገ ሩን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያጣል፤

እግዚአብሔር፣ ወኮነ ዕቅፍተ ወመ ስትተ ለሐዲስ ተክል ለእለ ነሥኡ ጥምቀተ ወዓዲ ለንኡስ ክርስ ቲያን ለዕድ ወለአንስት ከማሁ ክመ።

፴፱. ወእመሰ ኢመሀረ፣ወኢገሠጸ፣ ወኢሖረ በፍኖተ ርትዕ፣ ወንደገ ትእዛዛቲሁ ለእግዚአብሔር፣ ወበ እንተዝ ይረክብ ግዘተ፣ ወይ መጽእ ላዕሌሁ መቅሠፍተ እግዚአ ብሔር ፣ እስመ አስሐተ ፍኖቶሙ ለሕዝብ በክመ ስሕቱ ሕዝብ ዘበመዋዕለ ኢዮርብአም[፴፱]። ወእለ ተቀትሉ ምስለ ቆሬ[፴]።

፵. ወእመሰ ቦ ዘይኤብስ ዲበ ኤጳስ ቆጳስ ወላዕለ ሥዩማን እንዘ አልቦሙ አበሳ ወንጹሓን እሙ ንቱ፣ ኢይደልዎ ይባእ ቤተ ክር ስቲያኑ ለእግዚአብሔር፣ እስመ ደፈረ ወሖረ በእበድ በፍትወተ ነፍሱ ።

፵፩. ወበእንተዝ ይረክብ ዘረአ ቦሙ ለእለ ተማለቁ ላዕለ ኖኅ።[፴፩] ወበክመ አካን ዘነሥአ ለርእሱ ኅሩመ [፴፪]፣ ወበክመ ግያዝ ዘነሥአ ንዋየ እምኅበ ንዕማን ሶርያዊ *።

፴፱ ዘፍ.ነገ.፲፪.፳፱
፴. ዘኍ. ፲፮. ፵
፴፩ ዘፍ.፱. ፳፭-፳፮.
፴፪ ኢያ.፯.፩
፴፫.፪ኛ. ነገ. ፭. ፳፫

በእግዚአብሔርም ፊት በደልን ይሠራል፣ ጥምቀትን ለተቀበሉ አዲስ አማኞችም እንቅፋትና መሰናክል ይሆናል፣ ለወንዶችና ሴቶች ንዑስ ክርስቲያንም ፈጽሞ እንዲሁ ነው።

፴፱.ባያስተምርና ባይገሥጽ፣ በቅ ንነት መንገድም ባይሔድ፣ የእግ ዚአብሔርንም ትእዛዛት ቢተው፣ ስለዚህ ውግዘት ያገኛዋል፣ የእግ ዚአብሔር መቅሠፍት ይመጣበ ታል በኢዮርብአም ዘመን የነበሩ ሕዝብና ከቆሬ ጋር የተገደሉት እንደሳቱ የሕዝቡን መንገድ አሳስ ቷልና።

፵. በደል ሳይኖርባቸው ንጹሓ ንም ሲሆኑ በኤጲስ ቆጳሱ ላይ በሹማምንቱም ላይ የሚበድል ቢኖር ወደ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሊገባ አይገባውም፣ ደፍሮ በራሱ ፈቃድ በስንፍና ፍሬልና።

፵፩. ስለዚህም በኖኅ ላይ የተሣ ለቁ ሰዎች ያገኛቸውን ያገኛል፣ እርም የሆነውን ለራሱ እንደወ ሰደ እንደ አካን፣ ከሶርያዊው ከንዕማንም ገንዘብ እንደ ተቀበ ለው እንደ ግያዝ ይሆናል።

፲፪. ናሁኬ ይደልው ለኖላዊ አባ ግዕ ይምህር ወይገሥጽ በየውሃት፤ ወይሚጦሙ ውስተ ንስሓ ጠዪቆ ለለአሕዱ አሐዱ በሕይወቶሙ፤ ወይሥራዕ ንብረቶሙ በከመ ይደሉ በሰላም ከመ ይሕየዉ ሕዝብ ሠናየ ሕይወተ፤ ወይትመየጡ እምኀጣውኢሆሙ፤ ዝኬ ሥሙር በቅድመ እግዚአ ብሔር፤ እስመ ሰበ ተመይጠ ሰብእ እምኀጢአቱ ፤ ወገብአ ውስተ ንስሓ ርእዮሙ ኪያ዁ ይትሜህሩ ካልኣን ሠናየ አም ልኩ።

፲፫. ወበእንተዝ ይደልው ለኤጲስ ቆጶስ ይኩን ትጉህ ለገቢረ ሠናይ ከመ ይትዐወቅ ግብሩ በኀበ ኵሉ እስመ መርሖሙ ወኖላዊሆሙ ለሊቃውንት ወለመኳንንት፤ ወለመምህራን ወለኵሎሙ ዘእምታሕቴሁ።

፲፬. መፍትው ለኤጲስ ቆጶሳት ይንበሩ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ምስለ ካህናት፤ ወይፍትሑ ለለ አሐዱ አሐዱ በከመ ይደሉ፤ እስመ ሎሙ ወሀበ እግዚአብ ሔር ሥልጣነ፤ ወአዘዞሙ እንዘ ይብል «ዘአሰርክሙ በምድር ይኩን እሱረ በሰማያት፤ ወዘፈታሕክሙ በምድር ይኩን ፍቱሐ በሰማ ያት»[፴፬]።

[፴፬] ማቴ.፲፰.፲፰

፲፭. እነሆ የምእመናን ጠባቂ ያቸው በየውሃት ያስተምርና ይገሥጽ ዘንድ፤ እያንዳንዳቸ ውንም ተረድቶ በሕይወታቸው ወደ ንስሓ ይመልሳቸው ዘንድ ይገባዋል፤ ሕዝቡም መልካም ኑሮን እንዲኖሩ፤ ከኀጢአታቸ ውም እንዲመለሱ አነዋወራ ቸውን ያዘጋጅ ዘንድ ይገባዋል፤ ይህም በእግዚአብሔር ፊት የተ ወደደ ነው ፤ ሰው ከኀጢአቱ ተመልሶ ወደ ንስሓ ቢገባ ሌሎች እርሱን አይተው መል ካም አምልኮትን ይማራሉና ።

፲፮. ስለዚህም ለኤጲስ ቆጶሱ ሥራው በሁሉ ዘንድ እንዲታ ወቅ መልካም ሥራን ለመሥ ራት ትጉህ ይሆን ዘንድ ይገባ ዋል፤ ለሊቃውንቱና ለመኳን ንቱ፤ ለመምህራኑና ከበታቹ ላሉት ሁሉ መሪያቸውና ጠባቂያ ቸው ነውና።

፲፯. ኤጲስ ቆጶሳት ከካህናት ጋር በቤተክርስቲያን ተቀምጠው ለእ ያንዳንዱ እንደሚገባ ይፈርዱ ዘንድ ይገባል፤ እግዚአብሔር ለእነርሱ ሥልጣንን ሰጥቶአልና እንዲህም ብሎ አዘዞአቸዋልና «በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሁን፤ በምድርም የፈ ታችሁት በሰማያት የተፈታ ይሁን»።

፲፰. ርቱዕ ለኤጲስ ቆጶስ ይሚጦሙ ለሕዝብ ውስተ አእምሮ እግዚአብሔር ወይትወከፍ ንስሐ ሆሙ ለእለ ተመይጡ ኀበ እግዚአብሔር፤ ወይምሀሮሙ ወይና ዝዞሙ በተየውሆ ወበፍቅር፤ ወበፍሥሓ ልብ እስመ እግዚአብሔር አምላክ መሓሪ ውእቱ እስመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል ነቢይ።

፲፱. በሎሙ ሕያው አነ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር ከመ ኢይ ፈቅድ ይሙት ኃጥእ ዳዕሙ ከመ ይነስሕ ወይኅድግ ፍኖቶ እኪተ ወይሕየው»፤ ተመየጡ ተመየጡ፤እምፍናትክሙ እኩይ፤ ወለምንት ትመውቱ ቤተ እስራኤል።

፳. ወአንተ ወልደ ዕጓለ እመ ሕያው በሎሙ ለደቂቀ ሕዝብከ ጽድቁ ለጻድቅ ኢያድኅኖ አመ ይዜኂ፤ ወኀጢአቱ ለኃጥእ ኢያ ሐምሞ አመ ይኔስሕ እምኂ ጋዩ፤ ወጻድቅኒ ኢይድኅን እም ከመ አበሰ።

፳፩. ሶበ እቤሎ ለጻድቅ ሕይ ወት ተሐዩ ለእመ ተአመነ በጽ ድቁ ወገብረ ኀጢአተ፤ ኵሉ ጽድቆ ኢይዜክር ሎቱ፤ በኀጢ አቱ ዘገብረ ይመውት ።

፳፪. ኤጲስ ቆጶሱ ሕዝቡን እግ ዚአብሔርን ወደ ማወቅ ይመልሳቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትንም ንስሓቸውን ተቀ ብሎ በማለዘብ በፍቅርና በልብ ደስታ ያስተምራቸውና ያረጋጋ ቸው ዘንድ ይገባል፤ እግዚአብሔር መሓሪ አምላክ ነውና፤ እግዚአ ብሔር ለነቢዩ ሕዝቅኤል እንዲህ ብሎታልና።

፳፫. «እኔ ሕያው ነኝና ኀጢአ ተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕ ይወት ይኖር ዘንድ እንጂ፤ ኀጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈ ቅድም» ይላል ጌታ እግዚአ ብሔር፤ የእስራኤል ቤት ሆይ ተመለሱ፤ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ፤ ስለምንስ ትሞታላ ችሁ በላቸው ።

፳፬. አንተም የሰው ልጅ ሆይ፤ የሕዝብህን ልጆች እንዲህ በላ ቸው፤ «በበደለበት ቀን የጻድቅ ጽድቁ አያድነውም፤ኀጢአተኛም ከኀጢአቱ በተመለሰበት ቀን ኃጢአቱ አያሰናክለውም፤ ጻድ ቁም ኀጢአት ከሠራ በጽድቁ በሕይወት አይኖርም»።

፳፭. እኔ ጻድቁን በሕይወት ትኖ ራለህ ባልሁት ጊዜ እርሱ በጽድቁ ታምኖ ኀጢአት ቢሠራ በሠራው ኀጢአት ይሞታል እንጂ፤ ጽድቁን አላስብለትም።

፶፱. ወእምከመ እቤሎ ለኃጥእ ሞተ ትመውት ወነሸሐ እምኀጢአቱ ወገብረ ጽድቀ ወርትዐ።

፷. ወአግብአ አኀዘ፣ ወፈደየ ዘሂደ፣ ወክሕገ ሕይወት ሖረ፣ ወኢገብረ ኀጢአተ ሕይወተ የሐዩ፣ ወኢይመውት[፴፫] በኀጢአት ዘአበሰ ወኢይዜክር ሎቱ አባሳሁ ወጌጋዩ እስመ ገብረ ጽድቀ ወርትዐ ወቦቱ የሐዩ።

፷፩. ወበእንተዝ ይሴፈዉ ኃጥኣን እምከመ ተመይጡ እም ኀጣውኢሆሙ፣ ወነስሑ ይር ከቡ ተስፋ ሠናየ፣ ወእሙን ቱሰ ይወርስዋ ለምድር፣ ወእለ ኢአበሱ ይትዐቀቡ ከመ ኢይረዱ ውስተ ምንዳቤ ውበኳይ ወዝዘን።

፷፪. አእምርኬ ወለቡ አ ሰብእ እመ አበስከ ወገበርከ ኀጢአተ በዝ ዓለም ወኢነሳሕከ አልብከ ሕይወት፣ ወነስሕ እንከ እንዘ ሕያው አንተ፣ እስመ እምድኅረ ሞት አልቦ ንስሓ በከመ ይቤ ዳዊት «እስመ አልቦ በውስተ ሞት ዘይዜክረከ ወበሲኦልኒ መኑ የአምነከ[፴፬] ።

፴፫ ሕዝ ፴፫ ፡ ፲፭ - ፲፰
፴፬ መዝ. ፮ ፡ ፭ - ፮

፶፱. እኔም ኀጢአተኛውን ሞትን ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ እርሱ ከኀጢአቱ ተመልሶ ፍርድንና ቅን ነገርን ቢያደርግ፣

